# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 282 ሰኔ 12 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት

## ያለሥልጣኑ የቅጣት ክፍያ ተመን መመሪያ በማዘጋጀት ገንዘብ ሲሰበስብ መቆየቱ ተገለጸ

### - በሀገሪቱ የንግድ ሕግ መሠረት ንግድ ፈቃድ ካላወጣ ድርጅት ጋር ሲሠራ መቆየቱም ተጠቅሷል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ገንዘብ ለመሰብሰብ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ሳይኖረው የፓስፖርት ምዝገባ ቀነ ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦችን በቅጣት ለማስተናገድ የቅጣት ክፍያ ተመን መመሪያ አዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር በማጸደቅ 18 ሚሊዮን ብር ገደማ መሰብሰቡን የፌዴራል ዋና ኦዲተር አጋለጠ፡፡ አገልግሎቱ የፓስፖርት ሥራ ለመሥራት በሀገሪቱ የንግድ ሕግ መሠረት ንግድ ፈቃድ ካላወጣ እና በታክስ ሕጉ

የኢሚግሬሽንና ዜግነት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






# የዓባይ ግድብ

## ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ መገናኛ ብዙኃን ሚናቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ተጠየቀ

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የዓባይ ግድብ ግንባታ ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ መገናኛ ብዙኃን መረጃ የመስጠትና ህብረተሰቡን የማንቃት ሚናቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ የታላቁ ህዳሴ ግድብ ማስተባበሪያ ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ጠየቀ።

የዓባይ ግድብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# በዘንድሮ የመኸር እርሻ ከ20 ሚሊዮን ሔክታር በሳይ መሬት ይታረሳል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- በ2016/17 የመኸር ምርት ዘመን ከ20 ሚሊዮን ሔክታር መሬት በላይ መሬት እንደሚታረስ ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ እስከ ሰኔ ወር የመጀመሪያ ሳምንት ድረስ 14 ሚሊዮን ሔክታር መሬት የታረሰ ሲሆን ከ12 ሚሊዮን ሔክታር በላይ መሬት በኩታ ገጠም ለማልማትም እየተሠራ ነው፡፡

በዘንድሮ የመኸር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ተቋማቱ የሚያፈሩት የሰው ኃይል የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ትግበራ የተከተለ ሲሆን ይገባል

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

አዲስ አበባ፡- የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የሚያፈሩት የሰው ኃይል የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን የተከተለ ሊሆን እንደሚገባ ተገለጸ፡፡

በቴክኒክና ሙያ ኢንስቲትዩት፣ በጀርመን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅትና በሌሎችም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ትብብር የአረንጓዴ ኢትዮጵያ የቴክኒክና ሙያ ፎረም በትናንትናው ዕለት ተካሂዷል፡፡

የኢፌዴሪ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኢንስቲትዩት



ፎቶ፡- ሔዲሽ አብርሃ

ብሩክ ከድር (ዶ/ር)

ተቋማቱ የሚያፈሩት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

ገጽ 4

# ታጣቂ ኃይሎች አጀንዳቸውን ወደ ምክክር ቢያመጡ እንደሚያተርፉ ኢዜማ ገለጸ




# ኮሜሳ በአቪዬሽን መስክ የሴቶች ተሳትፎ ሊጎለብት እንደሚገባ አመላከተ

**አመለወርቅ ከበደ**

አዲስ አበባ፡-በአባል ሀገራቱ በሚገኙ የአቪዬሽን የሥራ መስኮች የሴቶች ተሳትፎ ሊጎለብት እንደሚገባ የምስራቅና ደቡባዊ አፍሪካ የጋራ ገበያ (ኮሜሳ) አስታወቀ፡፡

ኮሜሳ በአቪዬሽን ዘርፍ የሴቶችን እኩል የሥራ ተሳታፊነት ለማሳደግ ያለመ የሶስት ቀናት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰርቶ ማሳያ መርሃ ግብር ትናንት አስጀምሯል።

በኮሜሳ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሴክሬታሪያት ዳይሬክተር ቢያትሪስ ሲምዋፔንጋ፤ በሁሉም የስራ ዘርፎች የጾታ እኩል ተሳትፎ ቅድሚያ ተሰጥቶ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን ጠቁመው፤ በተለይ ደግሞ በአቪዬሽን መስኩ የሴቶች እኩል ተሳትፎ ወሳኝነት አለው ብለዋል።

ዳይሬክተሯ እንደገለጹት፤ በአየር መንገዶች በእንግዳ ተቀባይነትና በፍተሻ ሥራ ላይ ሴቶች በስፋት እየተሳተፉ ቢሆንም በሌሎች የሥራ አካባቢዎች ላይ ደግሞ በበቂ ሁኔታ የተሳትፎ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።

የጾታ ተሳትፎ በአንድ የሥራ ዘርፍ ብቻ ሊወሰን አይገባም ያሉት ዳይሬክተሯ፤ በአቪዬሽን ዘርፉ በመሠረታዊ የሥራ አካባቢዎች ላይ የሴቶች ተሳትፎ ማሳደግ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

በአዲስ አበባ የተጀመረው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሰርቶ ማሳያ መርሃ ግብር ዓላማው በአቪዬሽን ዘርፍ በሁሉም የሥራ አካባቢዎች ሴቶች እኩል ተሳታፊ እንዲሆኑ ማሽቻል ነው ብለዋል።

በአቪዬሽን ዘፍፍ የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ የተጀመረው ፕሮግራም ከሕግ አውጪዎችና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ምን እንደሚጠበቅ ግንዛቤ የሚሰጥበት መሆኑን አስረድተው፤ የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ሁሉም በቁርጠኝነት እንዲሰራ ይጠበቃል ሲሉ ተናግረዋል።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በአየር ትራንስፖርት አብራሪነት ሴቶች እየተሳተፉ ይገኛል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሴት ፓይለቶችን ቁጥር በማሳደግ በጎ ጅማሬዎችን ማሳየቱን አንስተዋል። የአየር መንገዱን አርዓያነት በመከተል ሌሎችም የሴቶችን ተሳትፎ ሊያጠናክሩ እንደሚገባ ጥሪ አቅርበዋል።

በሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የሴቶች ማብቃት ዘርፍ መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ አሸናፊ ፈይሳ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ በመዲናዋ የተዘጋጀው መርሃ ግብር በአቪዬሽን ዘርፉ ለሴቶች ምን አይነት ምቹ እድሎች እንዳሉ ለማሳየትና ሴቶች ዕድሉን ተጠቅመው እንዲያገለግሉ ለመደገፍ ይረዳል።

የሴቶች ተሳትፎ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ዝቅተኛ እንደነበር ያስታወሱት መሪ ሥራ አስፈጻሚው፤ አሁን ላይ በተለያዩ የሥራ መስኮች ሴቶች ይችላሉ የሚል እሳቤ እየዳበረ በመምጣቱ ተሳትፏቸውን ለማሳደግ የሚረዱ እንቅስቃሴዎች ተጠናክረው መቀጠላቸውን አመላክተዋል።

የሴቶችን እኩልነትና ተሳትፎ ከማሳደግ አንጻር ሚኒስቴሩ ፖሊሲዎችን በማዘጋጀት በመሥሪያ ቤቶች ያለውን አተገባበር እንደሚገመግም ተናግረዋል፡፡

ነገ በሚጠናቀቀው መርሃ ግበር ከዳግማዊ ምሊልክ እና ከእቴጌ መነን ትምህርት ቤቶች ለተውጣጡ 400 ሴት ተማሪዎች በአቪዬሽን ዘርፍ የግንዛቤ ሥልጠና እንደሚሰጥ ተገልጿል፡፡

# የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል መሙያ ሥርዓት ወደ ሥራ ሲገባ ነው

**ክፍለዮሐንስ አንበርብር**



አዲስ አበባ ፡- የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል መሙያ (EV-CHARGE) ሥርዓት እየተዘጋጀ ሲሆን በቅርቡ ወደ ሥራ ለማስገባት ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይቶችና የመመሪያ ሥርዓቶች እየተዘጋጁ መሆኑን የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለሥልጣን አስታወቀ።

የባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ አህመድ ሰይድ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል መሙያ (EV- CHARGE) ሥርዓት መመሪያን በተመለከተ በኃይሌ ግራንድ ሆቴል ከትናንት በስቲያ ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ ውይይት ላይ እንደተናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከነዳጅ ኃይል ከሚሰሩ ተሽከርካሪዎች በታዳሽ ኃይል ወደሚሰሩ ተሽከርካሪዎች እየተሸጋገረች ሲሆን ለዚህም የሚረዱ ዘርፈ ብዙ ተግባራት በመከናወን ላይ ናቸው።

ትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስቴርና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን መመሪያ ወጥቷል ያሉት አቶ አህመድ፤ በአሁኑም ወቅት የመጨረሻው ረቂቅ ላይ ውይይት ተደርጓል። በመቀጠል ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መመሪያውን ካፀደቀው በኋላ ወደ ፍትህ ሚኒስቴር በመላክ ወደ ሥራ የሚገባ ይሆናል፤ ለዚህም እየተነጋገርን ነው ፤ ስታንዳርድና ሕጎችን እንደ ባለሥልጣን የምናወጣ ሲሆን የሚመለከታቸው አካላት ደግሞ የሚጠበቅባቸውን እንዲወጡ የሚጠበቅብንን እየሠራን ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያ በየዓመቱ ነዳጅ ለማስገባት ከ 6 ነጥብ4 ቢሊዮን ዶላር በላይ እያወጣች መሆኑን የተናገሩት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ይህ በሀገሪቱ ላይ ከፍተኛ ጫና የሚያሳድር በመሆኑ ወደ ታዳሽ ኃይል መግባት አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመዋል።

ይህ ጉዞ ኢትዮጵያ የአየር ንብረት ብክለትን ለመከላከል የምታደርገው ጥረት አካል ሲሆን በወጪ ደረጃም በጣም አዋጭ መሆኑን ገልፀዋል። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ በርካታ የታዳሽ ኃይል አማራጭ ያላት ሀገር በመሆኗ ይህን ለመቀጠቀም መወሰኗ በሀገሪቱ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ጉልህ ሚና ይኖረዋል ብለዋል።

በነዳጅ እና ኢነርጂ ባለሥልጣን የብቃት ማረጋገጥና ቴክኒካል ሬጉሌሽን ቡድን መሪ ኢንጂነር ዳንኤል ስጦታው በበኩላቸው፤ መመሪያው ሀገሪቱ በየጊዜው እያሳየች ያለውን ዕድገት ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ጠቁመው፤ እንደአስፈላጊነቱ የታዳሽ ኃይል ሥራ ላይ ሲውል በሕግ እንዲመራ ሀገሪቱ ብሎም ዜጎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማሰብ ነው ሲሉም አስረድተዋል።

መመሪያው በኢትዮጵያ ውስጥ ለኤሌክትክ ተሽከርካሪ ኃይል ሙሌት አገልግሎት በሚሰጥ ወይም በሚጠቀም ማንኛውም ሰው አሊያም ድርጅት ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን፤ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች ያሉት መሆኑንም አመልክተዋል።

የውይይቱ ተሳታፊዎች በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ የታዳሽ ኃይል የሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎችን ለመጠቀም መወሰኗ እና ወደ ተግባር መግባቷ አስደሳች መሆኑን ገልፀዋል። ይሁንና ይህ ኢንቨስትመንት በዓይነቱ አዲስ በመሆኑ ማበረታቻዎች፣ አስቻይ መመሪያዎችና የሀገሪቱን መፃዒ ዕድሎችን ብሎም ቀጣይነት ያለው ኢንቨስትመንትን ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን በጥልቀት ሊመከርበት እንደሚገባ ጠይቀዋል።

# የለጋሾች ቁጥር ቢጨምርም የደም ፍላጎትን ከማማላት አንጻር ውስንነቶች አሉ

**በለጥሻቸው ልዑልሰገድ**



ጅማ፡- ባለፉት 20 ዓመታት የደም ለጋሾች ቁጥር እየጨመረ የመጣ ቢሆንም አሁንም የህክምና መስጫ ተቋማትን ፍላጎት ከማሟላት አንጻር ውስንነቶች እንዳሉ የኢትዮጵያ ደምና ህብረህዋሳት ባንክ አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ አሸናፊ አዘዘው ገለጹ።

በጅማ ከተማ በተከበረው 20ኛው የደም ለጋሾች ቀን ላይ በክብር እንግድነት ተገኝተው ንግግር ያደረጉት ዋና ዳይሬክሩ፤ ደም መለገስ የታማሚዎችን ሕይወት ማስቀጠል ብቻ ሳይሆን ከጀርባቸው ያለውን ቤተሰብ ተስፋ የማለምለም በጎ ተግባር ነው ብለዋል።

የኢትዮጵያ ደምና ህብረህዋሳት ባንክ አገልግሎት ደም ልገሳ የህብረተሰቡ አንድ የአገልግሎት አካልና ባህል ሆኖ እንዲቀጥልና በቂ የደም አቅርቦት እንዲኖር እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

አያይዘውም በክረምት ወቅት የሚፈጠረውን የደም እጥረት ለመቀነስ ትምህርተ ቤቶች በሚዘጉበት ወቅት የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት መጀመሩን ገልጸው በዚህ የደም ልገሳ ፕሮግራም ሁሉም ተሳታፊ እንዲሆን ጥሪያቸውን አቅርበዋል።

በፕሮግራሙ ላይ በመገኘት ንግግር ያደረጉት የኦሮሚያ ጤና ቢሮ ተወካይ አቶ ደረሰ አበራ በኦሮሚያ ክልል 13 የደም ባንኮች መኖራቸውን ገልጸው፤ ክልሉ በደም ልገሳ ማሰባሰብ ካለበት የደም መጠን ማግኘት የቻለው 30 በመቶ ብቻ መሆኑን ተናግረዋል።

ይህንን የደም እጥረት ችግር ለመፍታት የደም ልገሳ ፕሮግራሞችን ማስፋፋትና ማህበረሰቡ ስለደም ልገሳ ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑንም አሳስበዋል።

የደም ለጋሾች ቀን መከበር ዋና ዓላማም የደምን አስፈላጊነት በመረዳት ሁሉም ደም በመለገስ ሕይወት እንዲታደግ ግንዛቤ መፍጠር ነውም ሲሉ አክለዋል።

በየአመቱ ሰኔ 7 ቀን የሚከበረው 20ኛው የዓለም ደም ለጋሾች ቀን በጅማ ከተማ በተለያዩ የጎዳና ትርኢቶችና የምስጋና መርሃ ግብር ተከብሯል።

የዘንድሮ የደም ለጋሾች ቀን "ለ20 ዓመታት የደም ልገሳችሁ እናመሰግናለን" በሚል መሪ ቃል የተከበረ ሲሆን ክብረ በዓሉ እስከ ሰኔ 22 ድረስ በተለያዩ አካባቢዎች መከበሩን ይቀጥላል።



# በኦዲት ግኝት ተመላሽ እንዲደረግ አስተያየት ከቀረበባቸው የተመለሰው 11 በመቶ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በ2014 ዓ.ም 92 መሥሪያ ቤቶች በኦዲት ግኝት መሠረት ተመላሽ እንዲያደርጉ አስተያየት ከተሰጠበት 443 ሚሊዮን ብር እና 23 ሺህ ዶላር ውስጥ ተመላሽ የተደረገው ብር 48 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር ብቻ መሆኑን ዋና ኦዲተር አስታወቀ፡፡

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ትናንት ባካሄደው 32ኛ መደበኛ ስብሰባው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፋይናንስ ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርትን አዳምጧል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወ/ሮ መሠረት ዳምጤ ሪፖርቱን ለምክር ቤቱ ባቀረቡት ወቅት በተከናወኑ የኦዲት ሪፖርቶች መሠረት ርምጃ መወሰዱን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ የተገኘ ውጤት መሆኑንና አፈጻፀሙም 11 በመቶ ብቻ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

በ2015 ዓ.ም የኦዲት ውጤት ነቀፌታ የሌለበት 79፣ ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር አጥጋቢ ሆነው የተገኙ 50 እንዲሁም አስተያየት መስጠት ያልተቻለባቸው ሰባት የጎላ ችግር ያለባቸው ሆኖ በመገኘታቸው ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጣቸው 15 አጠቃላይ ውጤቱ ሲታይ ነቀፌታ የሌለበት ከጥቂት ጉድለቶች በስተቀር በአጠቃላይ አጥጋቢ ሆነው ተገኝተዋል፡፡

ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠባቸው የተወሰነ መሻሻል የታየበት ሆኖ መገኘቱም በሪፖርቱ ተጠቁሟል፡፡

የምክር ቤት አባላት በ2014 በጀት ዓመት በዋና ኦዲተር ብር ተመላሽ እንዲያደርጉ አስተያየት ተሰጥቶባቸው ተመላሽ ያላደረጉ ተቋማት ላይ ተጠያቂነት እንዲሰፍን አሳስበዋል፡፡

በባለበጀት መሥሪያ ቤቶች ርምጃ እስከመውሰድ የሚደርስ መሻሻሎች መኖራቸውን የጠቆሙት ወ/ሮ መሠረት ነገር ግን ተቀባይነት የሚያሳጣ የኦዲት ግኝት እና ብር ተመላሽ ያላደረጉ መሥሪያ ቤቶች ላይ ምክር ቤቱ ርምጃ እንዲወስድ ጠይቀዋል፡፡

ምክር ቤቱ በበኩሉ በ2014 በጀት ዓመት በዋና ኦዲተር በኦዲት ግኝት መሠረት ብር ተመላሽ እንዲያደርጉ አስተያየት የተሰጠባቸውና ተመላሽ ያላደረጉ ተቋማት ላይ ተጠያቂነት እንዲሰፍን አሳስቧል፡፡

ተመላሽ መደረግ ከነበረበት ገንዘብ መካከል ተመላሽ የተደረገው 11 በመቶ ብቻ መሆኑ ተገቢ አለመሆኑን የገለጹት የምክር ቤቱ አባላት በቀጣይም ገንዘቡን የማስመለስና ተጠያቂነትን የማስፈን ሥራ ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ አመልክተዋል፡፡

ወ/ሮ መሠረት በ2015 ዓ.ም መጠኑ ቢቀንስም የጥሬ ገንዘብ ጉድለት አሁንም የቀጠለ መሆኑን፣ የውዝፍ እና ተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ አለመሰብሰብ እና አለማወራረድ ችግሮች መኖራቸውን አመልክተዋል፡፡

በገቢ ግብር ቀረጥና ታክስ አዋጅ ደንብ እና መመሪያዎችን ያልጠበቁ ግዥዎችን፣ የውስጥ ገቢ አሰባሰብ እና አጠቃቀም የበጀት አስተዳደር እና አጠቃቀም በብልጫ የተከፈለ ክፍያዎች የመንግሥት ንብረት እና አስተዳደር የሚታዩ ጉድለቶች ዋና ዋና መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

ዋና ዋና ግድፈቶች ሆነው የተገኙትም፤ ሊዘረጉ የሚገባቸው የአሠራር ሥርዓቶች አለመዘርጋት እና አለመተግበር የተቋማት የቅንጅትና የትብብር ጉድለቶች መኖር፣ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው በጀት እና ጊዜ አለመጠናቀቅ፣ በእቅድ የተያዙ ሥራዎችን በእቅድ መሠረት አለመፈጸም ናቸው፡፡

በቀጣይ የምክር ቤት አባላት በተለይም የሚከታተሏቸው ቋሚ ኮሚቴዎች በሚመለከቷቸው ጊዜ በቁጥጥር እና ክትትል ታይቶ ችግሩ መፍትሄ እንደሚያገኝ ተስፋ አደርጋለሁ ብለዋል፡፡ የቁጥጥር ሥራው እንደሚጠናከርም ተስፋ እንዳላቸው ለምክር ቤት አባላቱ ተናግረዋል፡፡

# የማህጸን ጫፍ ካንሰርን የመከላከል ሥራዎች ተጠናክረው ቀጥለዋል

**መዓዛ ማሞ**



ሕይወት ሰለሞን (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- የማህጸን ጫፍ ካንሰር የህብረተሰቡ የጤና ችግር እንዳይሆን የሚከናወኑ የመከላከል ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠላቸውን የጤና ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

የማቲዎስ ወንዱ የኢትዮጵያ ካንሰር ሶሳይቲ 20ኛ ዓመት የምስረታ በዓል ማጠቃለያ መርሃ ግብር ትናንት ተካሂዷል።

በመርሃ ግብሩ ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በጤና ሚኒስቴር የበሽታ መከላከልና መቆጣጠር ዳይሬክቶሬት መሪ ሥራ አስፈጻሚ ሕይወት ሰለሞን (ዶ/ር)፤ በ2022 ዓ.ም የማህጸን ጫፍ ካንሰር በዓለም አቀፍ ደረጃ የህብረተሰቡ የጤና ችግር እንዳይሆን እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በሴቶች ላይ የሚፈጠረውን የማህጸን ጫፍ ካንሰር በሽታን ለመከላከል የልጃገረዶች ክትባት በስፋት እየተሰጠ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

የጤና ሚኒስቴር ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሥራዎች እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ሴቶች ላይ የሚከሰተውን የማህጸን ጫፍ ካንሰር ለመከላከል በተለያዩ አካባቢዎች የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አንስተዋል።

የጤና ሚኒስቴር ባለፉት ስምንት ዓመታት የካንሰር ሕክምናን ከማስፋፋት አንጻር ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት ለሕብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ጥረት ማድረጉን ተናግረዋል። ከትልልቅ ሆስፒታሎች ጀምሮ እስከ ጤና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም ድረስ ሕብረተሰቡን ያማከሉ ሥራዎች መጀመራቸውን ጠቁመዋል፡፡

በጥቁር አንበሳ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ብቻ ይሰጥ የነበረውን የጨረር ህክምና በማሳደግ በአራት ማዕከላት ሕክምናው እየተሰጠ መሆኑን አስታውሰው፤ በቅርቡም አገልግሎቱ ወደሰባት ማዕከላት ከፍ እንደሚል አስታውቀዋል። የካንሰር ህክምና ባለሙያዎች ቁጥርም እያደገ መምጣቱን አክለው ገልጸዋል፡፡

በመንግሥትና በጤና ተቋማት ብቻ የካንሰር ሕክምናን ማከናወን ከባድ መሆኑን የተናገሩት ዶክተር ሕይወት፤ እንደ ማቲዎስ ወንዱ አይነት ግብረሰናይ ማኅበራት ሊበራከቱና ሥራውን ሊያግዙ ይገባል ብለዋል።

የማቲዎስ ወንዱ ካንሰር ማኅበር የካንሰር ታማሚ ህፃናትና ወላጆችን በማገዝ ለሚሰራው ስኬታማ ሥራም ምስጋና አቅርበዋል፡፡

የማቲዎስ ወንዱ ካንሰር ሶሳይቲ መስራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ወንዱ በቀለ በበኩላቸው፤ ልጃቸው በህጻን ማቲዎስ በካንሰር በመሞቱ ምክንያት በገጠማቸው ኀዘን የጀመሩት በጎ ሥራ መሆኑን አስታውሰው፤ በ20 ዓመት ውስጥ በርካታ የካንሰር ታማሚ ህፃናት ወላጆችን የመድኃኒት፣ የትራንስፖርትና ልዩ ልዩ ወጪዎችን በመሸፈን እንዲሁም የማረፊያ ቤት በማዘጋጀት እገዛ እያደረጉ መሆኑን ጠቁመዋል።

የማቲዎስ ወንዱ ካንሰር ማህበር እያደረገ ያለውን መልካም ሥራ በመደገፍ ከማህበሩ ጎን የነበሩትን አመስግነው ፤ በቀጣይም ሁሉም ዜጋ የካንሰር ታማሚ ህጻናትና እና ወላጆቻቸውን እንዲደግፍ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡

በመርሃ ግብሩ ማህበሩን በ20 ዓመታት ቆይታው ላገዙ ለጤና ሚኒስቴር፣ ለምግብ መድኃኒት ባለሥልጣን እና ሌሎች መሰል ተቋማት እውቅና ተሰጥቷል።

# በትምህርት ቤቶች አካባቢ የተከፈቱ ሰባት ሺህ ጫትና ሺሻ ቤቶች ተዘግተዋል

**ሔርሞን ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- በበጀት ዓመቱ በትምህርት ቤቶችና ህፃናት በሚኖሩበት አካባቢ የተከፈቱ ሰባት ሺህ ጫትና ሺሻ ቤቶች እንዲዘጉ ማድረጉን የአዲስ አበባ ከተማ ደንብ ማስከበር ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

ባለሥልጣኑ በ2016 በጀት ዓመት ከቁጥጥር ጋር ተያይዞ የሠራቸውን ሥራዎች ከባለ ድርሻ አካላት ጋር ትናንት ገምግሟል፡፡

የባለስልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ሻለቃ ዘሪሁን ተፈራ በወቅቱ እንዳሉት፤ በትምህርት ቤቶች እና ህፃናት በሚኖሩበት አካባቢ የተከፈቱ ሰባት ሺህ ጫት ቤቶች እና ሺሻ ቤቶች እንዲዘጉ ተደርጓል፡፡

በአጠቃላይ የተሠራው ሥራ ሲታይ ውጤታማ ነው ያሉት ሻለቃ ዘሪሁን፤ ይህ ውጤት የተገኘው ከህብረተሰቡ ተሳትፎ እና ከባለ ድርሻ አካላት ቅንጅት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

የንግድ ቢሮ፣ የግንባታ ፈቃድ፣ የከተማዋ ፅዳት ኤጀንሲ እንዲሁም ሌሎች ባለ ድርሻ አካላት በቅንጅት በመሆን ያደረጉት አስተዋፅኦ እና አብሮነት የሚደነቅ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የባለሥልጣኑ አስተዳደር ዳይሬክተር አቶ ዳንኤል ቀፀላ ባቀረቡት ሪፖርት እንደተናገሩት፤ ሕገወጥ ንግዶችን ከማገድ ባለፈ ከዘጠኝ ሺህ በላይ ሕገ ወጥ ግንባታዎች እንዲቋረጥ ተደርጓል፡፡

በተጨማሪም ሰማንያ ዘጠኝ የሚጠጉ ሕገ ወጥ ስጋ ቤቶች ማዘጋት እንደተቻለ ጠቁመው፤ ባለሥልጣኑ ማሳካት ለሚፈልገው ዕቅድ በተለይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መሥራቱ ውጤታማ እንዳደረገው አስረድተዋል።

የቅድመ መከላከል ሥራዎች ከአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከበባት ጋር በመሆን መሠራቱን አስታውሰው፤ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ለሚሆን የትምህርት ማህበረሰብ አባላት ግንዛቤ ፈጥረናል ብለዋል።

ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ከግል ኮሌጆች እና ከማርኬቲንግ ተቋማት ጋር ውጤታማ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰዋል፡፡ በተለይ ከሚዲያዎች ጋር የተሠራው የግንዛቤ መስጫ ዝግጅቶች ተጠቃሽ እና የሚበረታታ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ከፅዳት ጋር ተያይዞ ከከተማዋ ፅዳት ኤጀንሲ ጋር በመሆን የጋራ ሥራዎች መሠራታቸውን ጠቅሰው፤ ከህብረተሰቡ ጤና እና ከሀገር ኢኮኖሚ አንፃር ችግሮች እንዳይከሰቱ በቅንጅት ሲሠራ ቆይቷል ብለዋል፡፡

በከተማዋ የሚገኙ ክፍት መሬቶች ወደ መሬት ባንክ እንዲመለሱም ሥራዎች መሠራታቸውን ተናግረዋል፡፡

ዜና

# ታጣቂ ኃይሎች አጀንዳቸውን ወደ ምክክር ቢያመጡ እንደሚያተርፉ ኢዜማ ገለጸ

ሄለን ወንድምነው

አዲስ አበባ፡- ታጣቂ ኃይሎች ለትጥቅ ያበቃቸውን አጀንዳ ወደ ሀገራዊ ምክክሩ ቢያቀርቡት ሁሉም አሸናፊ መሆን ይችላሉ ሲል የኢትዮጵያ ለዜጎች ማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ /ኢዜማ/ አሳሰበ።

የኢዜማ ፓርቲ ሥራ አስፈጻሚና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት የሴቶች ክንፍ ሰብሳቢ ቅድስት ግርማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ታጣቂ ኃይሎች ለትጥቅ ያበቃቸውን አጀንዳ ወደሀገራዊ ምክክሩ በማቅረብ ችግሮችን መፍታት ይገባል።

ታጣቂዎች ከእርስ በእርስ ግጭት፣ ከመገዳደልና ከአለመግባባት ባለፈ መንግሥትና ሥርዓት እንዲህ በድሎናል ብለው አጀንዳቸውን ወደ ሀገራዊ ምክክሩ በማምጣት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቢያሳውቁ ሁሉም አሸናፊ መሆን እንደሚችል አስታውቀዋል።



ቅድስት ግርማ

ጥያቄያቸውን በጠመንጃ ለማስመለስ የሚሞክሩ ኃይሎች በመዋጋት አትራፊና አሸናፊ መሆን ስለማይችሉ በሰላማዊ መንገድ የሚፈታበትን አማራጭ ሊከተሉ እንደሚገባ ገልጸዋል።

በሀገራዊ ምክክሩ አለመሳተፍ ቆመንለታን፣ እንታገልለታለን እና እንሞትለታለን የሚሉትን ህዝብ አጀንዳ ወደፊት ወጥቶ እንዳይፈታ ማድረግ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ ችግሮችን በመነጋገር፣ በመወያየትና በመመካከር በመፍታት ዘላቂ ሰላም ማስፈን እንደሚገባ ተናግረዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚዋ ገለጻ፣ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በመንግሥት የአሠራር ሥርዓትና በሌሎች ምክንያቶች በምክክሩ አንሳተፍም ይላሉ። ፓርቲዎች በሀገራዊ ምክክሩ በንቃት ቢሳተፉ ታግለው መቀየር የሚፈልጉትን የአሰራር ሥርዓትና አጀንዳ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ከመፍታት ባለፈ መንግሥትን ማስተማር ይችላሉ ብለዋል።

የመንግሥትና የፓርቲ አሠራር አንድ ላይ የተጣመረ በመሆኑ መንግሥትንና ገዢ ፓርቲን ለመለየት ችግር የሆነበት የአሠራር ሥርዓት መኖሩን ገልጸው፤ ይህንን እና መሰል ችግሮችን ወደ ሀገራዊ ምክክሩ በአጀንዳ መልክ በማቅረብ እንዲፈታ ማድረግ ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

ፓርቲዎች ከቀስቃሽ፣ ከሚያለያዩና ከሚያጋጩ አጀንዳዎች ራሳቸውን በማቀብ በየአካባቢው የሚነሱ ግጭቶችን ከመንግሥትና ከማሕበረሰቡ ጋር በመተባበር መፍታት ይገባል ብለዋል።

ለረጅም ዓመታት የውሸት ትርክት በመፍጠር፣ አንድ የሚያደርጉ ነገሮችን በመተው እና የሚያለያዩ አጀንዳዎችን በማብዛት እርስ በእርስ የተገዳደልንባቸው የደለቡ ችግሮች አሉ ያሉት ሥራ አስፈጻሚዋ፤ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ሁሉም ማህበረሰብ ንግግርን፣ ምክክርንና ውይይትን ባሕል ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል።

ሀገራዊ ምክክሩ ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት የእርስ በእርስ አለመግባባት፣ ግጭትና ጦርነት የሚያወጣ በመሆኑ ማንም ሰው በሀገራዊ ጉዳይ ላይ ባለማኩረፍ በንቃት በመሳተፍ የተረጋጋችና ሰላም የሰፈነባት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

## በዘንድሮ የመኸር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ኢሳያስ ለማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በዘንድሮ የመኸር እርሻ 20 ሚሊዮን 403 ሺህ 245 ሔክታር መሬት የታረሰ ሲሆን እስካሁን ባህላዊና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም 14 ሚሊዮን ሔክታር ገደማ መሬት ታርሷል።

ከታረሰው መሬት ውስጥ ሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን ሔክታር የሚጠጋ መሬት በዘር ተሸፍኗል ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ በዘር ከተሸፈነው መሬት ደግሞ ሁለት ሚሊዮን 69 ሺህ 153 ሄክታሩ በኩታ ገጠም የለማ መሆኑን ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በ2016/17 የመኸር ምርት ዘመን 12 ሚሊዮን 125 ሺህ በላይ ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም እርሻ እንደሚለማም አስረድተዋል።

በዘንድሮ የመኸር ምርት ዘመን በኩታ ገጠምና በመደበኛ ከሚሸፈነው ከ20 ሚሊዮን 403 ሺህ 245 ሄክታር መሬት ውስጥ ከ12 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በላዩን በክላስተር በማረስ 615 ሚሊዮን 921 ሺህ በላይ ኩንታል ምርት እንደሚጠበቅ ጠቁመዋል።

የበልግ እርሻ እንቅስቃሴ ሥራን በተመለከተ በ2016/17 ምርት ዘመን በበልግ አብቃይ በሆኑ አማራ ፣ ኦሮሚያ ፣ ትግራይ ፣ ሲዳማ ፣ ደቡብ ኢትዮጵያ ፣ ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ፣ ደቡብ ምዕራብና ሶማሌ ክልሎች ሶስት ሚሊዮን 123 ሺህ 797 ሄክታር መሬት በማልማት 81 ሺህ 852 ሺህ በላይ ኩንታል ምርት ለማግኘት መታቀዱን አመላክተዋል።

አቶ ኢሳያስ እንዳብራሩት፤ እስካሁን ድረስ በበልግ ሶስት ሚሊዮን 559 ሺህ 152 ሄክታር መሬት ታርሶ ሶስት ሚሊዮን 518 ሺህ 431 ሄክታር መሬት በዘር መሸፈኑን አስረድተዋል።

በዘር ከተሸፈነው መሬት ውስጥ በዘጠኝ ሰብሎች አንድ ሚሊዮን 96 ሺህ 312 ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም የተሸፈነ ሲሆን፤ በትግራይ ክልል 14 ሺህ 827 ሄክታር መሬት ተሰብስቦ 143 ሺህ 461 ኩንታል ምርት መገኘቱን ተናግረዋል።

ባለፈው የመኸር እርሻ አጠቃላይ ለማረስ ታቅዶ የነበረው 16 ሚሊዮን ሔክታር መሬት ሲሆን ከዚህ ውስጥ 8 ነጥብ 5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም ለመሸፈን ታቅዶ እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

## የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሠረት ግብር ከማይከፍል የግል ድርጅት ጋር ሲሠራ እንደነበርም ተጠቁሟል።

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሶስተኛ ዓመት 32 መደበኛ ስብሰባ የፌዴራል ዋና ኦዲተር የ2015 ዓ.ም የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት አዳምጧል።

ሪፖርቱን ያቀረቡት ዋና ኦዲተር ወይዘሮ መሠረት ዳምጤ፤ ተቋሙ ገንዘብ ለመሰብሰብ መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ሳይኖረው የፓስፖርት ምዝገባ ቀነ ቀጠሮ ያሳለፉ ግለሰቦችን በቅጣት ለማስተናገድ የቅጣት ክፍያ ተመን መመሪያ አዘጋጅቶ በዋና ዳይሬክተር በማጸደቅ ሕግ የጣሰ መሆኑን በሪፖርታቸው አመልክተዋል።

የመንግሥት የባንክ ሂሳብ የመክፈት እና የመዝጋት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን ሆኖ ሳለ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግለሰቦች ስም ከፍቶ ገቢ መሰብሰቡንም ነው ያመለከቱት።

በአጠቃላይ አካውንቱ ከተከፈተበት እ.ኤ.አ ከ01/09/2023 እስከ 29/01/2024 በአምስት ወራት 18 ሚሊዮን ብር ገደማ ወደ አካውንቱ ገቢ መደረጉን፣ ከዚህ ውስጥም ዘጠኝ ነጥብ ሶስት ሚሊዮን ብር ለትርፍ ሰአት ክፍያና ለበዓል ለሠራተኛው ስጦታ ወጪ መደረጉን በሪፖርቱ መለየቱን ይፋ አድርገዋል።

ለመንግሥት ሥራ የተሰበሰበን ገንዘብ ያለገንዘብ ሚኒስቴር ፈቃድ ወጪ የተደረገ መሆኑና እአአ በ29/01/2024 ስምንት ሚሊዮን 615 ሺህ በሂሳብ ደብተሩ ላይ ቀሪ መገኘቱንም ሪፖርቱ አመልክቷል።

ከዚህም ባሻገር የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ቪዲቸር (viditture) ከተባለ የግል ድርጅት ጋር ከመስከረም 06/2021 እስከ መስከረም 30 /2024 የሚቆይ በ28 /12/ 2013 የውል ስምምነት ማድረጉንም አስታውሰዋል። ድርጅቱ ከሀገር ውጭ ያሉ ነዋሪዎች ለፓስፖርት አገልግሎት ኦንላይን ሲያመለክቱ ሰነዱን አጣርቶ ወደኢምግሬሽን እና ፓስፖርቱ ተዘጋጅቶ ሲያልቅ ከኢምግሬሽን ተቀብሎ ወደ ደንበኛ ለማስተላለፍ ተገልጋዩ ከከፈለው በተጨማሪ 100 ዶላር እንደሚያስከፍል ኦዲቱ አጋልጧል።

ቪዲቸር የተባለው አስከፋዩ ድርጅት ይህንን ሥራ ለመሥራት የተመረጠበት መስፈርት፣ የግዢ ሂደት እና ፓስፖርትን ለማሰራጨት ፈቃድ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃም አላቀረበም።

የፓስፖርት ሥራ ለመሥራት በሀገሪቱ የንግድ ሕግ መሰረት ንግድ ፈቃድ ያላወጣ እና በታክስ ሕጉ መሠረት ግብር የማይከፍል ነው።

የኢምግሬሽንና ዜግነት አገልግሎትም በአዋጅ ቁጥር 1263/2014 እና በደንብ ቁጥር 449/2011 በተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ላይ የፓስፖርት አገልግሎትን በውክልና እንደሚሰጥ የተገለጸ ነገር ሳይኖር አገልግሎቱን ቪዲቸር ለተባለው የግል ድርጅት የሰጠ መሆኑን የዋና ኦዲተር ሪፖርት ይፋ አድርጓል።

የሠራተኞች የሥነምግባር መመሪያ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ጸድቆ ለሁሉም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች በመላክ ተግባራዊ አልተደረገም። የተቋሙ ሠራተኞችም ተገልጋዩን በአክብሮትና በትህትና የማያስተናግዱ መሆኑንም በኦዲት ሪፖርቱ ላይ ተቀምጧል።

የተቋሙ ሠራተኞች ከበር ጥበቃ ጀምሮ አስተባባሪዎችና አገልግሎት የሚሰጡ ኦፊሰሮች ተገልጋዩን የማመናጨቅ፣ አልባሌ ቃላት የመጠቀም፣ አልፎም የመጎተት፣ የመገፍተር እና የመማታት ሁኔታዎች መኖራቸውን የኦዲት ቡድኑ ባደረገው ምልከታ ማረጋገጡን ለማሳያ ያህል ቀርቧል።

ተቋሙ ለፓስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ የሚያገለግሉ የጸደቀ እና ወቅታዊ የሆነ መመሪያ፣ ስታንዳርድ እና የዜጎች ቻርተር የሌለው መሆኑም አስወቅሶታል።

ከድንበርና ከጎረቤት ሀገራት መሆናቸው አጠራጣሪ የሆኑ ተገልጋዮች ሲያጋጥሙ ዜግነታቸው የሚጣራበት መመሪያ የሌለው መሆኑ፤ ዜግነት የማጣራት ሥራውም በልምድ የሚከናወን፣ ውሳኔው ዜግነትን በሚያጣራው ግለሰብ መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ እና ወጥ የሆነ አሠራርን የማይከተል መሆኑ በኦዲት ግኝቱ ተለይቷል።

የአዲስ መደበኛ ፓስፖርት እና የፓስፖርት አገልግሎት ፈላጊዎች አገልግሎቱን በምን ያህል ጊዜ እንደሚያገኙ የተቀመጠ መመሪያ እና የጊዜ ሰሌዳ የሌለው፣ ፓስፖርት በቀነ ቀጠሮ የማይሰጥ፣ በቀጠሮ ያልደረሰላቸው ተገልጋዮች ማንን መጠየቅ እንዳለባቸው የሚገለጽበት አሠራር አለመኖር እና አገልግሎቱን በወቅቱ ማግኘታቸውን የማይከታተል መሆኑም በኦዲቱ ተመላክቷል።

## ተቋማቱ የሚያፈሩት ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ዋና ዳይሬክተር ብሩክ ከድር (ዶ/ር) በመድረኩ እንደተናገሩት፤ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የሚያፈሩት የሰው ኃይል ኢትዮጵያ የምትከተለውን የአረንጓዴ ኢኮኖሚ አቅጣጫን የተከተለ ሊሆን ይገባል።

የአረንጓዴ ቴክኒክና ሙያ ፅንሰ ሃሳብ በዋናነት የአየር ብክለትን ሊያስከትሉ የሚችሉ ችግሮችን መቀነስና አረንጓዴ አካባቢን መፍጠርን ማዕከል ያደረገ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል።

ዋና ዳይሬክተሩ እንደገለጹት፤ በግብርና፣ በግንባታ፣ በቱሪዝምና በሌሎችም የእድገት ተኮር ዘርፎች የሚከናወኑ ተግባራት የአረንጓዴ ኢኮኖሚ አቅጣጫን የተከተሉ እንዲሆኑ አስፈላጊውን የሰው ኃይል ማሰልጠን ይገባል።

በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች በሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎች የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ጽንሰ ሃሳብን መሠረት ያደረጉ ሰፋፊ ሥራዎች በመሠራት ላይ መሆናቸውንም አንስተዋል።

በኢትዮጵያ አረንጓዴ ኢኮኖሚን በተጨባጭ ተግባራዊ ለማድረግ በሚደረገው ጥረት ዋነኛው ችግር የሰው ኃይል ዝግጅት ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ የአረንጓዴ ቴክኒክና ሙያ ጽንሰ ሃሳብ ይህንን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል መሆኑን አመላክተዋል።

በሀገራችን በሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት በርካታ የሰው ኃይል መኖሩን አንስተው፤ ተቋማት ለኢንዱስትሪው የሰው ኃይልን ሲያዘጋጁ የሀገራችንን አረንጓዴ ልማት ማስቀጠል የሚችሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ አጽንኦት ሰጥተው ሊሰሩ ይገባል ብለዋል።

የአረንጓዴ ቴክኒክና ሙያን ተግባራዊ ለማድረግ መንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫን ከመቀየስ ጀምሮ ግንዛቤ የመፍጠር፣ ድጋፍ የማድረግና የማስተባበር ሚና አለው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፣ ይህንን ሚናውን እየተወጣ መሆኑንና ድጋፉ ይበልጥ እየተጠናከረ እንደሚሄድም አመላክተዋል።

የግንዛቤ ችግርና በሚመለከታቸው አካላት መካከል የቅንጅት ጉድለት መኖሩ እንደተግዳሮት የሚነሳ መሆኑን ተናግረው፤ ተግዳሮቶቹን ለመቅረፍ የሁሉም ትብብር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

ከ2 ሺህ 300 በላይ የአጫጭርና የረጅም ጊዜ ሥልጠና የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት መኖራቸውን ያነሱት ዶክተር ብሩክ፤ የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ወደ ተግባር ለመቀየር መነሻ የሚሆኑ የአረንጓዴ ቴክኒክና ሙያ ክበቦች መቋቋማቸውንም አስታውቀዋል። ክበባቱ በአመለካከት በኩል ለውጥ መፍጠራቸውን ገልጸዋል። እነዚህና ሌሎችም ጅምር ጥረቶችን ማስቀጠል ከተቻለ ኢትዮጵያ የምታወጣው የሠለጠነ የሰው ኃይል የአረንጓዴ ኢኮኖሚን ማሳካት የሚያስችል ይሆናል ብለዋል።

የጀርመን ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት ፕሮጀክት ማናጀር መሐመድ አሊ በበኩላቸው፤ የቴክኒክና ሙያ ዘርፍ የሚያፈራው ሰው ኃይል የአየር ብክለትን በመቀነስ ረገድ ወሳኝ ሚና እንዳለው አስረድተዋል።

ዘርፉ የሚያፈራው የሰው ኃይል ወደ ኢንዱስትሪው ሲገባ እንደ ውሃ፣ ኤሌክትሪክና ሌሎችንም ሀብቶች ቆጥቦ መጠቀም የሚያስችል አሠራሮችን በመፍጠር የተፈጥሮ ሀብትን ለቀጣይ ትውልድ የማስረከብና የአየር ብክለትን የመቀነስ ሚናውን ሊወጣ ይገባል ሲሉ ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ በአረንጓዴ ልማት የአካባቢ ጥበቃ እያከናወነች የሚገኘውን ስራ በበጎነት አንስተው፣ በየጊዜው እየጨመረ ከሚሄደው የሕዝብ ቁጥር አንጻር ተጨማሪ ሥራዎችን ማከናወን እንደሚገባ አመላክተዋል።

በጉባኤው ከተለያዩ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት የተውጣጡ ተማሪዎች የተሳተፉ ሲሆን የአረንጓዴ ቴክኒክና ሙያ ጽንሠ ሃሳብን ማዕከል ያደረጉ ጽሑፎች በቴክኒክና ሙያ ምሁራንና ተማሪዎች ቀርበዋል።

## የዓባይ ግድብ ቀሪ ሥራዎችን...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጽህፈት ቤቱ የዓባይ ግድብ ግንባታን በተመለከተ ከመገናኛ ብዙኃን አመራሮችና ባለሙያዎች ጋር በትናትናው ዕለት ውይይት አካሂዷል።

የጽህፈት ቤቱ ዋና ዳይሬክተር አረጋዊ በርሄ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደገለጹት፤ የግድቡን ግንባታ ለማጠናቀቅ በሚደረገው ጥረት የሚዲያና ኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች ጠንካራ ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ ሚናቸውን አጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል።

መገናኛ ብዙሃን ለዓባይ ግድብ ግንባታ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ በቀጣይ ግድቡን ለማጠናቀቅ በሚሠሩ ሥራዎች የበኩላቸውን ሚና መወጣት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

የዓባይ ግድብ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ነፃነትን የሚያጎናጽፍ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ ዜጎችን ከድህነት ለማውጣትና የዕድገት ጉዞን ለማፋጠን የሚረዳውን ግድብ ቀሪ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ርብርብ ማድረግ እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

መገናኛ ብዙሃን ግድቡ ለኢትዮጵያ ያለውን ጠቀሜታ በዘለቄታዊነት ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ማሳየት እንዳለባቸው አስረድተው፤ የግድቡን ታሪክ፣ የግንባታ ሂደት መሰነድ እና በስፋት ማስተዋወቅ እንደሚገባ ተናግረዋል።

የሚዲያ አካላት ከግድቡ ግንባታ ሂደት ጀምሮ እስካሁን ለነበራቸው የላቀ አስተዋጽኦ ምስጋና ያቀረቡት አረጋዊ ዶ/ር፤ የውይይት መድረኩ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ያላቸውን ተሳትፎ ለማጠናከር ታስቦ የተዘጋጀ መሆኑን ገልጸዋል።

የጽህፈት ቤቱ የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አለባቸው ሲሳይ በበኩሉ፤ የግድቡ ግንባታ ሂደት 96 በመቶ መድረሱንና በቀጣይ ሰባት ወራት ቀሪ አራት በመቶ የግድቡን ግንባታ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ የሚረዳ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን አስረድቷል።

የግድቡ ግንባታ በዜጎች ያላሰለሰ ጥረት በመገባደድ ላይ መሆኑን አስታውሶ፤ በቀጣይ ቀሪ 11 ተርባይኖች ወደ ሥራ ለማስገባት 45 ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ አስታውቋል።

ግድቡ በደለል እንዳይሞላ የአካባቢ ጥበቃና የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች ተጠናክረው መቀጠላቸውን ጠቁሞ፤ ለግንባታው እየተደረገ ያለው ድጋፍና የሕዝብ ተሳትፎ በተመሳሳይ ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ አመላክቷል።

ለ13 ዓመታት ኅብረተሰቡን ለግድብ ያለው ተሳትፎው የጎላ እንዲሆን ሲሠሩ የነበሩት የመገናኛ ብዙኃን ቀሪ ሥራውን ለማጠናቀቅ ጥረታቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉም ጥሪ ቀርቧል።

ግድቡ ትልቅ የዲፕሎማሲ ጥረትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነባር የዲፕሎማሲ ጥረቶች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸውም መልዕክት ተላልፏል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከቡናው ዘርፍ የበለጠ ተጠቃሚ ለመሆን !

መንግሥት ሀገሪቱ በግብርናው ዘርፍ ያላትን አቅም አሟጦ ለመጠቀም ሰፊ ሥራዎችን እያከናወነ ይገኛል። ግብርናው አጠቃላይ በሆነው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ካለው እና ሊኖረው ከሚችለው አስተዋጽኦ አንጻር የመንግሥት አሁናዊ ጥረቶች እንደሀገር ለጀመርነው ድህነትን በልማት የማሸነፍ ትግል እንደ ዋንኛ አቅም ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።

የግብርናው ዘርፍ ሀገሪቱ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለምታደርገው ጉዞ ካለው ስትራቴጂክ አስተዋጽኦ አንጻር ፤ መንግሥት አሁን ላይ ግብርናውን ከማዘመን ጀምሮ ተጨማሪ ለእርሻ የሚሆን መሬት በማስፋት ምርት እና ምርታማነትን ትርጉም ባለው መልኩ ለማሳደግ የሚያደርገው ጥረት በብዙ መልኩ ውጤታማ እየሆነ ነው።

በግብርናው ዘርፍ ባለፉት አምስት ዓመታት እንደ ሀገር ያስመዘገብናቸው ስኬቶች ፤ ሀገሪቱ ከነበረችበት ፈተና አንጻር ፤ ፈተናው ሊያስከትል ይችል የነበረውን የከፋ አደጋ መሻገር የቻልንበትን ዕድል ፈጥሯል፤ ከዚህም ባለፈ ዘርፉ የቱን ያህል ሀገርን ከደህነት ወደ ብልጽግና በማሻገር ሂደት ውስጥ ትልቅ አቅም እንዳለው በተጨባጭ አመላክቷል።

ለዚህም የበጋ የመስኖ ስንዴ ልማትን ጨምሮ በምግብ እህል ፤ በአትክልት እና ፍራፍሬ ዘርፎች እየተመዘገቡ ያሉ ውጤቶች ሀገርን ከፍተኛ ከሆነ የውጭ ምንዛሬ ወጪ መታደግ አስችለዋል ፤ ሀገሪቱ አጋጥሟት ከነበረው የሰላም ችግር አኳያ ከምግብ እህል አቅርቦት ጋር ሊፈጠር የሚችለውን አደጋ ለመቀልበስ አቅም ሆነዋል።

ከዚህም ባለፈ መንግሥት የፖሊሲ ትኩረት በመስጠት ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በሆነችባቸው የቡና እና የሻይ ቅጠል ልማት እየተመዘገበ ያለው ተስፋ ሰጪ ውጤት በግብርናው ዘርፍ ከሚካሄዱ ልማቶች ተጠቃሽ ነው።

በአንድ በኩል በመደበኛ የግብርና ሥራው ውስጥ በቡና እና የሻይ ቅጠል ልማት ትኩረት በመስጠት በልማቱ ተሳተፊ አርሶ አደሮች ጥራቱ የተጠበቀ ምርት በስፋት ለገበያ የሚያቀርቡበትን እድል እየፈጠረ ነው። የገበያ ትስስር እና የግብዓት አቅርቦቶችን በጊዜ የሚደርስበትን ሁኔታ እያመቻቸ ይገኛል።

በሌላ በኩል በተለይም በቡናው ዘርፍ ያለውን ምርታማነት ለማሳደግ ከመደበኛ የቡና ችግኝ ተከላ ባለፈ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር በሚሊዮን የሚቆጠር የቡና ችግኞችን በቡና አብቃይ አካባቢዎች በመትከል ፤ ዘርፉ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ያለውን ትርጉም ያለው አስተዋጽኦ ለማሳደግ እየተሠራ ነው።

ቡና አምራች ገበሬዎች የልፋታቸው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ እየተከናወነ ባለው ጠንካራ ሥራም ፤ አርሶ አደሩ በተናጠልም ሆነ በማኅበራቱ አማካኝነት ምርቱን ለዓለም ገበያ የሚያቀርብበት እድል በስፋት ተፈጥሯል ። በዚህም ማኅበራትን ጨምሮ ግለሰብ አርሶ አደሮች የገበያው የተሻለ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል።

በዚህም እንደ ሀገር ባለፉት ዘጠኝ ወራት ከቡና ኤክስፖርት አንድ ነጥብ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ማግኘት ተችሏል። ይህ በዘርፉ እየተመዘገበ ያለው ውጤት በራሱ አበረታች ቢሆንም ፤ ሀገሪቱ ለቡና ምርት ካላት ተስማሚ አየር ፤ ተፈላጊ የቡና አይነቶች እና የቡና መገኛ ሀገር ከመሆኗ አኳያ ገና ብዙ በመሥራት ብዙ ተጠቃሚ መሆን ይገባል።

በተለይም ሀገሪቱ በዓለም አቀፍ የቡና ገበያ በጥራት እና ብዛት አሸንፋ እንድትወጣ ፤አምራች የኅብረተሰብ ክፍል ለቡና ጥራት ተገቢውን ጥንቃቄ እንዲያደርግ የሚያስችል ሰፊ የግንዛቤ ሥራዎችን መሥራት ያስፈልጋል ። ችግኞችን ከመትከል ጀምሮ ምርቱን በመሰብሰብ እና በማከማቸት ፤ ወደ ውጪ በመላክ ሂደት ውስጥ በምርቱ ጥራት ላይ ሊፈጠሩ ለሚችሉ ችግሮች ተገቢውን ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል።

በምርቱን ወደ ውጪ በመላክ ሂደት የሚያጋጥሙ የሎጂስቲክ እና ቢሮክራቲክ ችግሮችን ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ በመቅረፍ ፤ ምርቱ በፍጥነት ወደ ገበያ የሚቀርብበትን አሠራር ከፍ ባካለ የተጠያቂነት ሥርዓት ጋር ማስፈን ያስፈልጋል።

የቡና ምርት ላይ እሴት በመጨመር ወደ ውጭ ለመላክ የሚደረጉ ጥረቶችን አግባብ ባለው መንገድ ማበረታታት ፤ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሃይልን በስፋት ለማፍራት የሚደረጉ ጥረቶችም ሆኑ በቡና ላይ የሚደረጉ ምርምሮች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ መደገፍ ፤ ለዚህ የሚሆን ሥርዓት ማበጀት ይገባል።

በተለይም ቡና አምራች በሆኑ አካባቢዎች ያሉ ዩኒቨርሲቲዎች ለጉዳዩ ትልቁን ኃላፊነት ወስደው መንቀሳቀስ፤ ምርቱ በዓለም አቀፍ ገበያ የተሻለ ተወዳዳሪ የሚሆንበትን ጥራት ከማስጠበቅ አንስቶ፤ የተለያዩ ሀገራዊ የቡና ምርቶችን በሁለንተናዊ መልኩ በማስተዋወቅ ረገድ የሚጠበቅባቸውን መወጣት ይጠበቅባቸዋል።

ከዚህም ባለፈ በዘርፉ የሚከሄዱ የምርምር ውጤቶች፤ ፈጥነው ወደ ተግባር የሚሸጋገሩበትን የአሠራር ሥርዓት መፍጠር ፤ በዘርፉ ጥናት ለማካሄድ የሚፈልጉ ተመራማሪዎችን በማበረታታት እና በመደገፍ ይህንን ትልቅ ሀገራዊ ሀብት ወደ ተጨባጭ ልማት መለወጥ ያስፈልጋል፡፡

አዲስ ዘመን
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## በጎ ፈቃደኝነትን ለሰላም!

**ሙዘይን ዘኢትዮጵያ**

በጎ ፍቃደኝነት ሰዎች ትርፍ ወይም ጥቅም ሳይፈልጉ በራሳቸው ተነሳሽነት ሌሎችን ለማገዝ የሚያከናውኑት ተግባር ነው:: ይህን በጎ ተግባር ሰዎች በራሳቸው ፍቃድ ሲያከናውኑ ታዲያ ዘርን፣ ፆታን፣ የቆዳ ቀለምን፣ ሃይማኖትን፣ ቋንቋንና ፖለቲካን መሠረት አድርገው አይደለም::

በዓለም አቀፍ ደረጃ ቁጥራቸው የበዛ በጎ ፍቃደኞች እንደየፍላጎታቸው በየጊዜው በተለያዩ ዘርፎች ላይ ይሳተፋሉ:: በኢትዮጵያም ቀደም ሲል ስለ በጎ ፍቃደኝነት አገልግሎት በህብረተሰቡ ዘንድ ያለው ግንዛቤ አነስተኛና በመንግሥት በኩልም የተሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ የነበረ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ በዚህ አገልግሎት የሚሳተፉ ሰዎች ቁጥር እየጨመረ መጥቷል::

በዚህ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከሚሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ ወጣቶች የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ:: እስካሁንም በርካታ ወጣቶች በተለያዩ የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ውስጥ በመሳተፍ የዜግነት ግዴታቸውን ተወጥተዋል:: በዚህም በርካታ ዜጎች በልዩ ልዩ መልኩ ከበጎ ፍቃድ አገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ችለዋል::

በዚህ የክረምት ወቅትም በርካታ ወጣቶች በልዩ ልዩ መስኮች በበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ውስጥ በስፋት ይሳተፋሉ ተብሎ ይጠበቃል:: አምናና ካችአምና በነበረው መረጃ መሠረትም በአረንጓዴ ዐሻራ፣ የአካባቢ ጥበቃ፣ ሰላም፣ መንገድ ደህንነት፣ የጤና አጠባበቅ ሥራዎች፣ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቀረት ግንዛቤ በመፍጠርና በሌሎችም የክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሥራዎች ላይ ተሳትፈዋል::

የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት፣ የአረጋውያንና አቅመ ደካማ ቤት እድሳት፣ ሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውርን መከላከልና ግንዛቤ መፍጠርም ወጣቶቹ ከተሳተፉባቸው የበጎ ፍቃድ ሥራዎች ውስጥ በተጨማሪ የሚጠቀሱ ናቸው::

ከዚህ ቀደም ወጣቶች ከተሳተፉባቸው የበጎ ፍቃድ አገልግሎቶች ውስጡ አንዱና ዋነኛው የሰላም ጉዳይ እንደሆነ ይታወሳል:: ከሶስትና አራት ዓመታት በፊት በተለይም በሰሜኑ ጦርነት ምክንያትና በሌሎችም የሀገሪቱ አካባቢዎች በተከሰቱ ግጭቶች የሰላምና ፀጥታ መደፍረስ ተከስቷል::

በጦርነቱ ወቅትና ጦርነቱ በስምምነት እስከተቋጨበት ጊዜ ድረስ የሀገሪቱን ሰላምና ፀጥታ ወደነበረበት ለመመለስ በርካታ ጥረቶች ሲደረጉ ቆይተዋል:: ጦርነቱ በስምምነት ከተቋጨ በኋላ በመንግሥትና በህወሓት በኩል የገፅ ለገፅ ግንኙነት ተደርጓል:: በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምት መሠረት መንግሥትና ህወሓት የስምምነቱን አፈፃፀሙን ገቢራዊ ሲያደርጉ ቆይተዋል::

ከዚሁ ጎን ለጎን ታዲያ ሁሌም ቢሆን የሀገሪቱ ሰላምና ፀጥታ ሲደፈርስ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የግጭቶች ሰለባ የሚሆነው ወጣቱ ነውና ሰላምን በማስፈን ሂደት የወጣቱ ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑ አያጠያይቅም:: ለዛም ነው ባለፉት ዓመታት በመላው ሀገሪቱ ወጣቶች በሰላም ዙሪያ ውይይት እንዲያደርጉና ለሰላም መስፈን የበኩላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ በክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎትና በሌሎችም እነርሱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሲሳተፉ የቆዩት::

በዋናነት ደግሞ የወጣቶችን እርስ በርስ ግንኙነቶች እንዲጠናከሩና አጠቃላይ የወጣቶች ተሳትፎ የጎላ ሚና እንዲኖረው በሰላም ዙሪያ ያተኮሩ ግንኙነቶችም ተካሂደዋል:: አሁንም ሰላም ቅድሚያ የሚሰጠው የሀገሪቱ አጀንዳ ነው:: ምንም እንኳን አቅማቸው እየተሸመደመደ ቢመጣም በኦሮሚያና በአማራ ክልል የሚንቀሳቀሱ ታጣቂ ቡድኖች አሁንም የአካባቢያቸውን ፀጥታና ሰላም እየነሱ ነው:: አልፎ አልፎም ቢሆን በሌሎች አካባቢዎች ላይ ግጭቶችና አለመስማማቶች ሲከሰቱ ይሰማል::

እንዲያም ሆኖ ግን መንግሥት ባደረጋቸው የሰላም ውይይቶችና በወሰዳቸው የማረጋጋት እርምጃዎች ግጭቶች በሚስተዋልባቸው በአማራ፣ በኦሮሚያ፣ በጋምቤላና ቤኒሻንጉል ክልሎች አንፃራዊ ሰላም ሰፍኗል:: ሕዝቡም በሰላም ወጥቶ በሰላም መግባት ችሏል:: ገበሬው ወደ እርሻው ተመልሷ:: ነጋዴውም ንግዱን አጧጡፏል:: ተማሪዎችም ወደ ትምህርት ገበታቸው ተመልሰዋል::

የሚፈለገው አስተማማኝ ሰላም በኢትዮጵያ እንዲረጋገጥ ከተፈለገ ግን በይበልጥ ወጣቱ ላይ አተኩሮ መሥራት ያስፈልጋል:: በተለይ አሁን አብዛኛው ወጣት የትምህርት ጊዜውን አጠናቆ ወደየቤቱ የሚመለስበት ጊዜ እንደመሆኑ ይህን ጊዜ በደምብ መጠቀም ይገባል:: አብዛኛው ወጣት የትርፍ ጊዜውን ማህበራዊ ሚዲያዎችን እየተጠቀመ እንደሚያሳልፍ ይገመታል::

የማህበራዊ ሚዲያዎችን ሲጠቀም ደግሞ አንዳንዴ ትክለኛ ባልሆኑ መረጃዎችና ትርክቶች ጭንቅላቱ ተሞልቶ ለግጭት ሊነሳሳ ይችላል:: ነገሮችን በሰከነና በበሰለ መንገድ በማት የማህበራዊ ሚዲያዎችን በበጎ መልኩ የሚጠቀም ከሆነ ደግሞ በተቃራኒው የሰላም ዘብ ይሆናል::

ስለዚህ ወጣቱ በዚህ ክረምት ወቅት ባለው ትርፍ ጊዜ ማህበራዊ ሚዲያውን በበጎ በመጠቀም ለሰላም ዘብ መጠበቅ የራሱን አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል:: ይህ በቀጥታ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ውስጥ ሳይሳተፍ በራሱ አስተዋፅኦ የሚያደርገው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሥራ ሊሆን ይችላል::

ወጣቱ ትኩስ ሃይልና ብዙ ነገሮችን መፍጠር የሚችል እንደመሆኑ ማህበራዊ ሚዲያውን በመጥፎ መንገድ በመጠቀም ምድርን እንደሚያናውጥ ሁሉ ይህን መንገድ ትቶ ስለሰላም በመዘመርና በመስበክ ለሰላምና ፀጥታ መጠበቅ የራሱን አስተዋፅኦ ማድረግ ይችላል:: ይህ ሲባል ግን ወጣቱ ያሉትን ጥያቄዎች አይጠይቅ፤ መብቱንም አያስከብር ማለት አይደለም:: ይህንኑ አጋጣሚ በመጠቀም ጥያቄዎቹን በሰላማዊ መንገድ ማንሳት ይችላል::

ስለዚህ ወጣቱ ለሰላምና ፀጥታ መረጋገጥ እንዱና በራሱ ተሳሽነት የሚያደርገው ነገር ማህበራዊ ሚዲያውን በመጠቀም ስለሰላም መስበክ ሆኖ ሳለ የክረምት ወቅቱን ተከትሎ መንግሥት ወጣቶችን በማሰባሰብ በሚያካሂደው የወጣቶች ክረምት የበጎ ፍቃድ አገልግሎትም በመሳተፍ ለሰላም መረጋገጥ የድርሻውን መወጣት ይችላል::

በዚህ የክረምት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በርካታ ወጣቶች በሰላም ጉዳይ ይወያያሉ ተብሎ ይጠበቃል:: የእርስ በርስ ግንኙነቶችን ለማጠናከር የሚያስችሉ ጉዞዎችም እንደሚደረጉ ይታመናል:: ስለዚህ በዚህ ክረምትም ወጣቶች በእንዲህ አይነቱ ውይይትና የሰላም ጉዞ ላይ በስፋትና በንቃት መሳተፍ ይጠበቅበታል::

ይህ የክረምት የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ወጣቱ ቁጭ ብሎ ስለሰላም የሚነጋገርበት መድረክ ነው:: ሃሳቡን የሚለዋወጥበትና የሃሳብ አሸናፊነት ምን ያህል ከጠመንጃ ሃይል የበለጠ ገዢ መሆኑን የሚያይበት ነው:: የሰላም ዋጋዋ ከፍ ያለና ከሰላም የሚገኘው በረከትም ምን ያህል ለእርሱ ጠቃሚ መሆኑን የሚረዳበት አጋጣሚ ነው::

በሰከነና በሠለጠነ መንገድ ተነጋግሮና ተወያይቶ መፍትሄ ላይ መድረስ እንደሚቻል የሚገነዘብበትም ጭምር ነው:: ከዚህ አንፃር ወጣቱ መንግሥት በሚያመቻቸው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በተለይ በሰላም ጉዳይ ላይ ተሳትፎ በማድረግ ለሰላም መጠበቁ የበኩሉን ድርሻ ማበርከት ይጠበቅበታል::

በተለይ ደግሞ ሀገራዊ ምክክሩ ወጣቱን በስፋት የሚያሳትፍና ከአጀንዳ ማሰባሰብ ወደ ምክክር ሂደት እየተሸጋገረ በመሆኑ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ወጣቱ ስለሀገሩ ሰላም መምከር ይኖርበታል:: በርግጥ ወጣቱ አሁንም ድረስ ያልተመለሱ በርካታ ጥያቄዎች እንዳሉት ይታመናል::

ስለዚህ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ስለሰላም ከመስበኩ በዘለለ ወጣቱ በሀገራዊ ምክክሩ ያሉበትን ጥያቄዎች ማንሳት ይኖርበታል:: መንግሥትም ለወጣቱ ጥያቄዎች አጥጋቢ መልስ ለመስጠት መዘጋጀት ይኖርበታል::

የሀገሪቱን ሰላምና ደህንነት ለማስጠበቅ ወሳኝ ከሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ውስጥ አንዱና ዋነኛው ወጣቱ እንደመሆኑ መንግሥትም ለወጣቱ ትኩረት ሰጥቶና በክረምቱ የወጣቶች የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የሰላም ውይይት መድረክ በማመቻቸት ወጣቶች ሃሳባቸውን እንዲተነፍሱና ለሰላም መጠበቅ የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፉ የበኩሉን ድርሻ መወጣት ይጠበቅበታል::

የወጣቶች የእርስ በእርስ ግንኙነቶችም ለሰላም መምጣት የራሳቸው አስተዋፅኦ ስላላቸው ወጣቶች ወደተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተጓጉዘው እርስበርስ እንዲወያዩ፣ አንዳቸው የሌላቸውን ባህል እንዲያውቁና እንዲማማሩ፣ ስለ ሰላም እንዲሰብኩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርበታል::

ወጣት ላይ መሥራት የነገ ትውልድ ላይ መሥራት ነው:: ወጣት ላይ መሥራት የነገዋን ኢትዮጵያ መገንባት ነው:: ወጣት ላይ መሥራት ሀገርን በሁለንተናዊ መልኩ መቀየር ነው:: እናም ወጣት ሆይ በክረምት ስለ ሰላም ዘምር:: ስለሰላም ዘክር:: ስለሰላም አውራ::

ያኔ ወደቀጣዩና ትክክለኛው የሕይወት መስነመርህ ትገባለህ:: መንግሥትም ወጣት ላይ ሥራ:: ለወጣቶች መወያያና መነጋገሪያ የሚሆኑ መድረኮችንና ሁኔታዎችን አመቻች:: ያኔ የሀገርን ሃላፊነት ተሸክመው ለቀጣዩ ትውልድ አደራ የሚያስተላልፉ ወጣቶችን ማፍራት ትችላለህ!!

## ፍረዱኝ

# "በሕይወት በሌለች እናታችን ስም የፍርድ ውሳኔ በማሰጠት ቤታችን ሊነጥቁን ነው"

\- አርቲስት ምናሉሽ ረታ

መክሊት ወንድወሰን እና ሞገስ ተስፋ

አመልካች ወይዘሮ ፋንታዬ ባዩ ወልደየስ ተጠሪዎች ከወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ እና ሻምበል ታረቀኝ ገ/ሕይወት እና ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ የዛሬው የፍረዱኝ ዓምድ ዝግጅታችን በኦሮሚያ ክልል ሸገር ከተማ አስተዳደር ቡራዩ ከተማ የቤት ቁጥር 198 ከሆነ ቤት ጋር ተያይዞ የተፈጠረን ውዝግብ ያስመለክተናል።

« እናታችን ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በ1988 ዓ.ም ሕጋዊ አካሄድን ተከልሎ የወይዘሮ ሣህለወርቅ ባዩ ሕጋዊ ወራሽ ከሆኑት ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ እና ሻምበል ታረቀኝ ገ/ሕይወት ከተባሉ ሰዎች የውርስ ቤት ገዝታ ነበር። ይህ በእንዲህ እንዳለ በ1996 ዓ.ም ወይዘሮ ጤናዬ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች። ይህን ተከትሎ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በ1988 ዓ.ም ገዝታው የነበረው ቤት ለአምስት ልጆቿ በውረስ ተላለፈ። ይሁን እንጂ በ2007 ዓ.ም የእኛ ነው ባይ ሰዎች መጡ። የእኛ ነው ባዮች እናታችን በሕይወት እንደሌለች እያወቁ እናታችንን በመክሰስ ፍርድ ቤት መቅረብ ባለመቻላቸው በሌሉበት አስፈርደናል በሚል የፍርድ ቤት ውሳኔ ያዙ። በውሳኔው መሰረትም በውርስ ያገኘውን ቤት እንወስዳለን አሉ። ይህን ተከትሎ የወይዘሮ ጤናዬ ወራሾች ጉዳዩን ወደፍርድ ቤት ወስደን ብንከራከርም ቤቱን ለከሳሽ እንዲሰጥ የሚል ውሳኔ ተወሰነ ። ይህ ትክክል አይደለም ብለን ብንከራከርም ሰሚ አጥተናል። የተፈጸመብን በደል የኢትዮጵያ ሕዝብ አይቶ ፍረደን» ስትል አርቲስት ምናሉሽ ረታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የመልካም አስተዳደርና የምርመራ ቡድን አቤት ብላለች።

የኢትዮጵ ሕዝብ ግራ ቀኙን አይቶ መፍረድ እንዲችል የዝግጅት ክፍላችን በጉዳዩ ላይ ጥልቀት ያለው ምርመራ አድርጓል። ያገኘውን የምርመራ ውጤት በሁለት ክፍሎች ሸክፎታል። የመጀመሪያውን ክፍል እንዲህ አቅርቦታል። መልካም ንባብ ።

**ከቅሬታ አቅራቢዋ አንደበት**

በደል ተፈጽሞብናል ስትል ለዝግጅት ክፍላችን አቤት ያለችው አርቲስት ምናሉሽ ረታ ትባላላች። እንደ አርቲስት ምናሉሽ ገለጻ፤ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በ1988 ዓ.ም ሕጋዊ ወራሽ ከሆኑት ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ እና ሻምበል ታረቀኝ ገብረ ሕይወት ቡራዩ ከተማ ገፈርሳ ቀበሌ የቤት ቁጥር 198 ቤት የተመዘገበ 324 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ቤት ገዝታ በሕይወት እስከተለየችበት እስከ 1996 ዓ.ም ድረስ በስሟ በሕጋዊ መንገድ አስመዝግባ ስትገለገልበት ቆይታለች። ወይዘሮ ጤናዬ በ1996 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ስትለይ ልጆቿ ማለትም አርቲስት ምናሉሽ ረታ፤ አቶ አሸናፊ ረታ፤ አቶ አለማየሁ ረታ፤ ወይዘሮ ሕይወት ረታና አቶ ኤርሚያስ ረታ በሕጋዊ መንገድ በፍርድ ቤት በማሳወጅ አሁን ውዝግብ የተነሳበትን ቤት ወረሱ። በእናታቸው ስም የንግድ ቤት በመክፈት መስራት ጀመሩ። ወራሾች በስራ መደራረብ ምክንያት የንግድ ስራቸውን ማከናወን ባለመቻላቸው ቤቱን በሕጋዊ ውል ለሌላ ነጋዴ በማከራየት ሲጠቀሙበት መቆየታቸውን ታስረዳለች።

ነገር ግን ሕጉን ተከትለን ወራሽነት አሳውጀን የተረከብውን ንብረት እነ ፋንታየ ባዩ የተባሉ ሰዎች በሕይወት የሌለች እናታቸውን በሕይወት እንዳለች በማስመሰል እና በፍርድ ቤት በመክሰስ እንዲሁም እናታቸው በሕይወት ኖረው ነገር ግን ፍርድ ቤት ለመቅረብ ፈቃደኛ እንዳልሆኑ በማስመሰል የፍርድ ቤት ውሳኔ አስወሰኑ። ውሳኔውን መሰረት በማድረግ ቤቱን እንዲያስረክቧቸው የውሳኔ አፈጻጸም ማምጣታቸውን አቤቱታ አቅራቢዋ ታስረዳለች።

የአቤቱታ አቅራቢዋ ወላጅ እናት ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በህጋዊ መንገድ አሳውጇ እና ወርሳ ስትጠቀምበት ከነበረች ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ ግለሰብ በመግዛት ከቡራዩ ከተማ አስተዳደር የመሬት ይዞታ ጽህፈት ቤት ሕጋዊ ሰነድ ተሰጥቷቸዋል። የአፈር እና የቤት ግብር እየገበሩ ሲጠቀሙበት መኖራቸውን የሰነድ እና የሰው ምስክር እንዳላት ትገልጻለች።

እንደ አርቲስት ምናሉሽ ገለጻ፤ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በ1988 ዓ.ም የገዙትን ቤት በስማቸው ከአዞሩ በኋላ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በተለምዶ አብነት ተብሎ ከሚጠራው ሰፈር የነበራቸውን ቤት በመሸጥ ቡራዩ ከተማ በገዙት ቦታ ላይ ቤት ወቅቱን በሚመጥን መልኩ በድንጋይና መሰል ቁሳቁሶች በማነጽ የሆቴል ንግድ ስራ እየሰሩበት እንደቆዩ ታስረዳለች።

ክሱ ከመቅረቡ በፊት ከሙዚቃ ስራ ጋር በተያያዘ ቡራዩ ከሚገኘው የእናቷ ቤት ወጥታ እንደነበር የገለጸችው አርቲስት ምናሉሽ፤ በቤቱ ወንድሞቿ፤ አንድ እህቷ እና እናታቸው ሲኖሩበትና የንግድ ስራ ሲሰሩበት እንደነበሩ ታስረዳለች።

‹‹ኑሮ ኑሮ ከሞት ዞሮ ዞሮ ከቤት›› ያለችው አርቲስት ምናሉሽ በ1996 ዓ.ም እናታቸው ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ከዚህ ዓለም በሞት መለየታቸውን ትናገራለች። ከ1996 እስከ 2000 ዓ.ም ወንድሞቿ እየተቀያየሩ ቤቱን ያስተዳድሩት ጀመር። ይሁን እንጂ የንግድ ቤቱ በእናታቸው ስም ጤናዬ በዳሶ መታሰቢያ ተብሎ ይሰራ እንደበር ታስረዳለች። ይህ በእንዲህ እንዳለ በ2000 ዓ.ም እስካሁን በሕይወት በሌሉት በናታችሁ ስም ግብር ስትገብሩ ቆይታችኋል። ይህ አሰራር ትክክል ስላልሆነ ንግድ ፈቃዱን በስማችሁ አዙሩ የሚል አስገዳጅ ትዛዝ ከንግድ ቢሮ መጣ ። ይህን ተከትሎ የወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ወራሽ ልጆች በራሳቸው ስም ንግድ ፈቃድ ለማውጣት ተንቀሳቀሱ። በወቅቱ ንግድ ፈቃድ የሚሰጠውና ፈቃድ የሚያዞረው አምቦ ከተማ ስለነበር እናታቸው መሞታቸውን በማሳወጅ የንግድ ፈቃዱን ስም ቀየሩ። ይሁን እንጂ የአቤቱታ አቅራቢዋ ወንድሞች በቤቱ የነበራቸውን የንግድ ስራ አቋረጡ። 2006 ዓ.ም በቡራዩ ከተማ ፍርድ ቤት በሕጋዊ መንገድ የንግድ ቤቱን ሌላ ሰው አከራዩ። ከንግድ ቤቱ በጀርባ ያለውን ቤት ደግሞ አንድ ወንድማቸው ብቻ ለመኖሪያነት ይጠቀምብት እንደነበር ትናገራለች።

ይህ በእንዲህ እንዳለ 2007 ዓ.ም ሐምሌ ወር ላይ ቤቱ የእኛ ነው ፤ ልቀቁ የሚሉ ሰዎች የፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘው መጡ የሚሉት አቤቱታ አቅራቢዋ ጉዳዩን ለማጣራት ሞክረው በወቅቱ በሕይወት በሌሉ እናታቸው ላይ ፍርድ ማረፉን እንደተመለከቱ ይናገራሉ።

አቤቱታ አቅራቢዋ እንደገለጸችው፤ የፍትህ ጉድለት መፈጠር የጀመረው ምንም አይነት መጥሪያ በሌለበት እና በሕይወት የሌለችውን እናታቸው በሕይወት እንዳለች አድርጎ በመክሰስ ከሳሾች ፍትህ ለማግኘት የሄዱበት ርቀትና ፍርድ ቤቶችም ብይን የሰጡበት አግባብ ነው።

"ፍርድ ቤት ተከሳሽ ባልቀረበበት እና በሕይወት በሌሉ ተከሳሽ ላይ እንዴት ውሳኔ ሊሰጥ ቻለ?" ስትል አቤቱታ አቅራቢዋ ትጠይቃለች። በሕይወት በሌለ ሰው ላይ የተሰጠን ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ማሳረፉ ተገቢነው ብላ እንደማታምን ገልጻ፤ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ ከመወሰኑ በፊት የሟችን ሕጋዊ ወራሾች ጠርቶ ማከራከር እንደነበረበት ትገልጻለች።

"መጥሪያ ሳይሰጥ ውርስ ሳይጣራ ሙት ይከሰሳል? ቤቱን የሸጠችው ሴትዮ ሕጋዊ ወራሽነቷን በምን አይነት መንገድ ነው ያስነሱት? ስትሸጥ ደግሞ ከባሏ ጋር ሆና ነው የሸጠችው። ባሏም ተከሳሽ ሆኖ ነው የቀረበው። በሷ ደግሞ ሞቷል። እሱም አልቀረበም። እንዴት ነው ሙት የሚከሰሰው? እኛ ተከሰን ወራሽነታችን ላይ ተከራክረናል ወይ? የወይዘሮ ጤናዬ ወራሾች አምስት ነን አንዳችን ቀርበን ነበር ወይ?" ስትል አቤቱታ አቅራቢዋ ትናጋራለች።

ዘግይተውም ቢሆን በሟች እናታቸው ላይ ብይን መሰጠቱትን ሰሙ ሕጋዊ ወራሽ ልጆች ጉዳዩን ወደ ፍርድ ቤት ወሰዱት። ፍርድ ቤትም በሟች ላይ ያስፈረዱትን ወይዘሮ ፋንታዬ ባየ እና ሕጋዊ ወራሾችን አከራከረ። በሟች ላይ ያስፈረዱትን እነ ወይዘሮ ፋንታየ ባዩን "ቤቱ የእናንተ ስለመሆኑ ፍርድ ቤት ወስኗል። ፍርድ ቤቱ የእናንተ ስለመሆኑ ለመወሰን የሄደባቸው ሂደቶችን የሚያሳዩ ሰነዶችን አቅርቡ?" ተብለው ተጠየቁ። ነገር ግን እነ ወይዘሮ ፋንታየ ባዩ "እኛ ሂደቱን የሚያሳይ ሰነድ የለንም፡ ያለን የፍርድ ቤቱ ውሳኔ ብቻ ነው" ሲሉ ምላሽ መስጠታቸውን አርቲስት ምናሉሽ ትናገራለች። ይህን ተከትሎ አርቲስት ምናሉሽም ከሳሽ ወይዘሮ ፋንታየ ከፍርድ ቤቱ ውሳኔው ባሻገር ቤቱ የእነሱ ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ጉዳዩ የታየበትን ሂደት እርቀት የሚያሳዩ ሰነዶች ማቅረብ ነበረባት። ነገር ግን የፍርድ ሂደቱን ባልቀረቡበት አግባብ እንዲከራከሩ ፍርድ ቤት መፍቀዱ በእራሱ ትክክል አለመሆኑን ታስረዳለች።


ከሳሽ ወይዘሮ ፋንታየ በውሳኔው መሰረት ቤቱን ሊረከቡ በመጡበት ወቅት አንድ ወንድማቸው ብቻውን በቤቱ ይኖር እንደነበር ያስታወሱት አቤቱታ አቅራቢዋ፤ የንግድ በቱን በፍርድ ቤት ያከራዩት የወይዘሮ ጤናዬ ሕጋዊ ወራሾች እያሉ ነጋዴው ወይዘሮ ፋንታየ የፍርድ ቤት ውሳኔ ይዘው ሲመጡ በመፍራት በሰፈር ውል ኪራይ መዋዋሉን እና ለኪራዩም ከገንዘብ ሰጥቶ እንደነበር ታስረዳለች። ይህን ተከትሎ የወይዘሮ ጤናየ ህጋዊ ወራሾች እነ ወይዘሮ ፋንታየን ከሰሱ። ፍርድ ቤቱም እነ ወይዘሮ ፋንታየን ኪራይ መቀበል እንደማይችሉ ውሳኔ አሳረፈ።

ቤቱ የእኛ ነው ባይ ሰዎች መምጣታቸውን ተከትሎ አርቲስት ምናሉሽ እና ቤተሰቦቿ ጠበቃ ቀጥረው ክርክር ጀመሩ። ጉዳዩ እስከ ሰበር ደረሰ። ጉዳዩ ሰበር ላይ እያለ ከሳሽ ወይዘሮ ፋንታየ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየች ። ከሳሽ ስትሞት ቤተሰቦቿ እናታቸውን ወክለው ተከራከሩ። ሰበር ላይ ችሎቱ በጉዳዩ የሕግ ግድፈት አይቼበታለሁ አጣሩና ዝጉ አሉ። ጉዳዩ በድጋሚ እንዲጣራ ተደረገ። በተደረገው ማጣራት ቤቱ የወይዘሮ ጤናዬ ወራሾች ስለመሆኑ ውሳኔ ተሰጠበት። ለውሳኔ ወይዘሮ ፋንታየ ቤተሰቦች እንዲቀርቡ ታዘዙ። እንዲቀርቡ በየሰፈራቸው መጥሪያ ተለጠፈ። የሚቀርብ ሲጠፋ ሁለት ጊዜ በጋዜጣ ታወጀ። ነገር ግን ችሎት የሚመጣ ጠፋ።

ውሳኔ አግኝቶ ፋይሉ ከተዘጋ በኋላ ቤቱ የነበረበት ቦታ በመንገድ ምክንያት ሲፈርስ 2 ነጥብ 8 ሚሊዮን ብር ገዳማ የካሳ ክፍያ ለሕጋዊ ወራሾች ተከፋፍሎ ተሰጣቸው። ከካሳ ክፍያው በተጨማሪ ካርታ ያለው መሬት በስማቸው ተሰጡ። ይህ በእንዲህ እንዳለ በክርክር ተረተው በጋዜጣ ጭምር ሲፈለጉ የነበሩ የወይዘሮ ፋንታየ ቤተሰቦች "መሬቱ የተሰጠን ለእኛ ነው። ገንዘቡ መሰጠት ያለበት ለእኛ ነው፡፡" የሚል ክስ ይዘው መጡ። ይህን ተከትሎ ፍርድ ቤቱ ስለጉዳዩ ሳያጣራ የክርክር መዝገብ ቁጥሩን እንዲቀይሩ አዘዘ። ቁጥሩ ከተቀየረ በኋላ ጉዳዩ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሄደ። ይህን የወይዘሮ ጤናዬ ወራሾች ለምንድነው ቁጥሩን የሚቀየረው? ሲሉ ፍርድ ቤቱን ጠይቀው እንደነበር ታስረዳለች ።

የፋይል ቁጥሩ ከተቀየረ በኋላ የፍርድ ሂደቱ በሙሉ መልኩን ቀየረ የምትለው አርቲስት ምናሉሽ ፤ ፍርድ ቤቱ በካሳ የወሰዳችሁትን ገንዘብ መልሱ፤ የወንድሞችሽ የወሰዱትን ገንዘብ የምታመጭው አንችው ነሽ የሚል ውሳኔ እንደተላለፈባት ታስረዳለች።

"570 ሺ ብር አካባቢ በእያንዳንዳችን የባንክ ሂሳብ ቁጥር የካሳ ብር ገብቷል። በእናቴ ድርሻ መጠየቅ






ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# ፍረዱኝ

## “በሕይወት በሌለች እናታችን ስም የፍርድ. . .

ከገጽ 6 የዞረ





Caffee Oromiyaatti Biiroo Daldalaa fi Tu...

Waraqaa ragaa Galmeessa Guddaa

ካለብኝም መጠየቅ የሚገባኝ የደረሰኝን ገንዘብ እንጂ የሁሉን ድርሻ ክፈይ መባሉ ፍትሐዊ አይደለም” ስትል መጠየቋን ነገር ግን ሰሚ አለማግኘቷን አቤቱታ አቅራቢዋ ታስረዳለች።

**የሰነድ ማስረጃዎች**

**ሰነድ አንድ፡-** ይህ ሰነድ የወልመራ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሚያመላክት ነው። የወልመራ ፍርድ ቤት አመልካች ወይዘሮ ሕይወት ረታ፤ አቶ አሸናፊ ረታ፤ አቶ አለማየሁ ረታ፤ ወይዘሮ ምናሉሽ ረታ እና አቶ ኤርሚያስ ረታ እናታቸው ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በቀን 06/02/1996 ዓ.ም ማረፋቸውና በቀን 07/02/1996 ቀብራቸው መፈጸሙን በማስረጃ ተጠርቶ ውሳኔ እንዲሰጣቸው ለወልመራ ወረዳ ፍርድ ቤት በማመልከቻ ጠይቀዋል። ፍርድ ቤቱም አስፈላጊውን የሰውና ሌሎች ማስረጃዎችን ካጣራ በኋላ በዳኛ ታደሰ በየነ አማካኝነት አመልካቾች የወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ሕጋዊ ወራሽ መሆናቸው በፍትሐብሔር ሕግ አንቀጽ 842 (1) ጠቅሶ ውሳኔ አሳልፏል። ይህን ውሳኔ ተከትሎ ሕጋዊ ወራሾች በወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በሕጋዊ ሰነድ ተመዝግቦ የሚገኘውን ቤት ወርሰው ሲጠቀሙ ከ20 ዓመታት በላይ መሆኑን በሰነዱ ተመላክቷል።

**ሰነድ ሁለት፡-** ስለከተማ ቦታ አሰራርና አጠቃቀም በወጣው አዋጅ ቁጥር 292/78 አንቀጽ 9 መሰረት መጠኑ በግልጽ ተለይቶ ለወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በይዞታ እንዲጠቀሙበት መሰጠቱን በቁጥር ቡ/ል/28/88 መገለጹን እና ካርታ መሰጠታቸውን ሰነድ ያሳያል። በተጨማሪም የኦሮሚያ መሬት ልማትና ማኔጅመንት ኤጀንሲ « የኪራይ መሬት የይዞታ የምስክር ወረቀት በሚል የወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ የዓምስቱ ልጆች ፎቶ ያለበት 324 ካሬ ሜትር ቦታ የተረከቡበት ሰነድ መኖሩ ያሳያል።

**ሰነድ ሶስት፡-** በቀን 02/ 03/1989 ዓ.ም የተጻፈ የድርጅት ቤት ሽያጭ ውል ስምምነት እንደሚያሳየው ውል ተቀባይ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ከውል ሰጭዎች ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለና ከሻምበል ታረቀኝ ገብረ ሕይወት በኦሮሚያ ክልል ወልመራ ወረዳ ልዩ ቀበሌ ገፈርሳ ቡራዩ ውስጥ የሚገኝ የቤት ቁጥር 198 የቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ቢዩአር 28/88 በሆነው የተመዘገበ እና የቦታው ስፋት 324 ካሬ ሜትር ላይ ያረፈ ቤትን በ35 ሺ ብር ለውል ተቀባይ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ መሸጡንና የቤቱን ሰነድ ለውል ተቀባይ ማስረከባቸውን ሰነዱ ያትታል።

በሰነዱ ላይ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ፍትህ ቢሮ የሕግ ባለሙያዎች እና የውልና ማስረጃ ምዝገባ መምሪያ ቁጥር ደብሊውኤ/1989/77 በጽህፈት ቤቱ ቀርውበው መፈራረማቸውና የሕግ ባለሙያዎች መምሪያ የውልና ማስረጃ ምዝገባ ኃላፊ በቀን 24/6/1989 ዓ.ም ዲሳሳ ድሪብሳ በፊርማቸው ያረጋገጡበት ማስረጃ ያሳያል፡፡

**ሰነድ አራት፡-** ይህ ሰነድ ወይዘሮ ፋንታዬ የሀሰት ሰነድ ብለው ካቀረቡት የሰነድ ማስረጃ መካከል አንዱ ነው። ከሳሽ በጠበቃቸው አማካኝነት ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጳውሎስ ምድብ ፍታብሔር ችሎት በቀን መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም በተጻፈ ማመልከቻ እንደሚያስረዳው አመልካች ወይዘሮ ፋንታዬ ባዩ ወልደየስ ተጠሪዎች ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ፤ ሻምበል ታረቀኝ ገብረ ሕይወት እና ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ወራሽ አቶ አሸናፊ ረታ አቤቱታው በፍርድ ቤቱ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 9 መሠረት ተሻሽሎ የቀረበ እና የሶስተኛ ተጠሪ ወራሽ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ከኛ እና ከ2ኛ ተጠሪዎች ጋር ሻጭና ገዥ ሆነው በሕዳር 2 ቀን 1989 ዓ.ም ያደረጉት የቤት ሽያጭ ውል ፈርሶ ውሉ ቀሪ እንዲሆን አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የአመልካች እህት የነበሩት ወይዘሮ ሣህለወርቅ ባዩ በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ አጠራር ወረዳ 18 ቀበሌ 02 በአሁኑ አጠራር ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 15/16 የቤት ቁጥር 068 ውስጥ ሲኖሩ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት መጋቢት 27 ቀን 1987 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት እንደተለዩ በመጠቆም የአመልካች የሟች እህቴ የወይዘሮ ሣህለወርቅ ባዩ ወራሽ መሆኔን በፍርድ ቤት አረጋግጩ የሟች እህቴን የውርስ ሀብት ለመያዝ ስሞክር ሟች አቶ ግዛቸው በቀለ እና አንደኛ ተጠሪ ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ ሚያዚያ 18 ቀን 1987 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ለፍርድ ቤት አቅርበው ሟች ወይዘሮ ሣህለወርቅ ባዩ በሕይወት በነበሩበት ወቅት ጥር 14 ቀን 1986 ዓ.ም በተፃፈ የስጦታ ውል ሰነድ አማካኝነት ንብረታቸውን ሰጥተውኛል የስጦታ ውሉ ፀድቆ ማስረጃ ይሰጠኝ በማለት የሐሰት ሰነድ ለፍርድ ቤቱ አቅርበው ባሰጡት ውሣኔ የሟች አውራሽ እህቴን ንብረት በመሉ ይዘው ሊያስረክበኝ ፈቃደኛ አልነበሩም የሚል አቤቱታ ቀርቧል፡፡

አቶ ግዛቸው በቀለ እና አንደኛ ተጠሪ ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ ለፍርድ ቤት አቅርበው ያፀደቁት የስጦታ ውል በሐሰት የተዘጋጀ ሰነድ እንጂ ሟች ወይዘሮ ሣህለወርቅ ባዩ የፈረሙበት የስጦታ ሰነድ አይደለም የሚል መቃወሚያ አመልካች ፍርድ ቤት አቅርቤ ክርክሩ ሲታይ ቆይቶ ሐምሌ 2 ቀን 2002 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስጦታ ውል ተብሎ ለፍርድ ቤቱ የቀረበው ሰነድ ሟች ወይዘሮ ሣህለወርቅ ባዩ ያስፈረሙበት የሀሰት ሆነ በፎረንሲክ ምርመራ ስለተረጋገጠ ፍርድ ቤቱ ሰጥቶት የነበረው የስጦታ ሰነድ የማጽደቅ ውሣኔ ቀሪ አድርጓል። በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ የሐሰት ሰነድ ለፍርድ ቤት አቅርበው በማፀደቅ በተሰጠው ውሣኔው አማካኝነት በቡራዮ ከተማ የሚገኘውን የቤት ቁጥር 198 የሆነውን ቤት በይዞታቸው ስር አድርገው ስለነበር ቤቱን እንዳይሸጡ እንዳይለውጡ በፍርድ ቤት እግድ ትእዛዝ ተሰጥቶበት ከክርክር ላይ እያለ አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ምንም ሕጋዊ መብት ሣይኖራቸው ከላይ ቁጥሩ የተጠቀሰውን ቤት ለሦስተኛ ተጠሪ አውራሽ ለወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ለመሸጥ ተስማምተው ሕዳር 2 ቀን 1989 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ሰነድ አማካኝነት ተዋውለው ለሶስተኛ ተጠሪ አውራሽ ለወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ማስተላለፋቸውን ከክፍለ ከተማው ማዘጋጃ ቤት ማወቅ እንደቻሉ አመልካች ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፍትሐብሔር ችሎት እንደጠየቁ ያሳያል፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች የሽያጭ ውሉ የተዋዋለበት ንብረት ባለሀብት አለመሆናቸውን እያወቁ የሦስተኛ ተጠሪ አወውራሽ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ በንብረቱ ላይ መቃወሚያ ቀርቦ ጉዳዩ በፍርድ ቤት በክርክር ላይ መሆኑን እና ቤቱ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ የእግድ ትእዛዝ የተሰጠበት መሆኑን እያወቁ የግዥ ውል ተዋውለው ቤቱን ተረክበዋል። ይህም ውል ከሕግ ውጭ የተደረገ ውል ከመሆኑም በላይ የአመልካችን የወራሽነት መብት የሚጋፋና የንብረት ባለቤትነት መብት የሚያሳጣ ውል ስለሆነ ሊፈርስ ይገባዋል፡፡

ስለዚህ የሦስተኛ ተጠሪ አውራሽ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ከ1ኛ እና ከ2ኛ ተጠሪዎች ከሕግ አግባብ ውጭ በቡራዩ ከተማ ውስጥ በሚገኘው የቤት ቁጥር 198 በሆነው ቤት ላይ ሕዳር 2 ቀን 1989 ዓ.ም የተዋዋሉት ውል እንዲፈርስ ሲሉ አመልካች ማቅረባቸው ያሳያል፡፡

በተመሳሳይ ቀን አመልካች ወይዘሮ ፋንታዬ ባዩ ወልደየስ በቀን መጋቢት 12 ቀን 2005 ዓ.ም ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጳውሎስ ምድብ ፍታብሔር ችሎት 1ኛ ተጠሪዎች ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ፤ ሻምበል ታረቀኝ ገብረ ሕይወት፤ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ወራሽ አቶ አሸናፊ ረታ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 223 መሠረት በቀረበ የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ፣ አመልካች በ12/07/2005 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ አሻሻልኩት ብለው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ በሐምሌ 12 ቀን 2003 ዓ.ም ጽፌ ባቀረብኩት የክስ አቤቱታ ያቀረብኩት የማስረጃ ዝርዝር መግለጫ አሁን ተሻሽሎ ላቀረበው ክስ ማስረጃዬ ስለሆነ ቀድሞ የቀረበው ማስረጃ ለተሻሻለውም ክስ በማስረጃነት እንዲመዘገብልኝ ብለው ማቅረባቸውን ያስረዳል፡፡

**ሰነድ አምስት፡-** ይህ ሰነድ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ የያዘ ነው። የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በቀን 20/05/2007 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 34211 በዳኛ አመሃ ታደሰ ከሳሽ ወይዘሮ ፋንታዬ ባዩ በጠበቃቸው አሰልፈው ገብረ መስቀል አንደኛ ወይዘሮ ተስፋነሽ በቀለ፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ሻምበል ታረቀኝ ገብረህይወትና ሶስተኛ ተከሳሽ በሕይወት የሌሉት ወይዘሮ ጤና በዳሶ የቀረበ ክስ ላይ የሰጠው ፍርድ በቡራዩ ከተማ የቤት ቁጥር 198 የሆነው ቤት አንደኛና ሁለተኛ ተከሳሾች መብት ሳይኖራቸው ለሶስተኛ ተከሳሽ በሽያጭ ማስተላለፋቸው ተከትሎ ውሉ እንዲፈርስ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚገልጽ ሲሆን ውሳኔው ቤቱ ሙሉ ይዞታ ለከሳሽ ከሟች ሳህለወርቅ ባዩ በውርስ የተላፈ በመሆኑ ከሳሽ ሕጋዊ ባለሙብት ናቸው። 3ኛ ተከሳሽ ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ከ1ኛ እና 2ኛ ተከሰሶች ኅዳር 02/03/1989 ዓ.ም ያቋቋሙት ቡራዩ ከተማ አስተዳደር የቤት ቁጥር 198 ላይ ውል ፈርመዋል። ስለሆነም ውሉ በመፍረሱ ከሳሽ ሙሉ በሙሉ ይዞታው ከወይዘሮ ጤናዬ ይረከቡ የሚል ውሳኔ መወሰኑን ያመላክታል።

**ሰነድ ስድስት፡-** የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቀን ሰኔ 30/ 2009 ዓ.ም በቁጥር የሰ/መ/ቁ.13975 በዳኛ ጸጋይ አስማማው፤ ሙስጠፋ አህመድ፤ አብርሃ መሰለ፤ ጳውሎስ ኦርሺሶ እና ሰናይት አድነው በተሰየመ ችሎት እነ ወይዘሮ ምናሉሽ በወከሉት ጠበቃ ምትኩ አልማው አማካኝት ቀርበው ወይዘሮ ፋንታዬ ባዩ በሌሉበት፤ ሻምበል ታረቀኝ ገብረ ህይወት በሌሉበት የሟች ወይዘሮ ጤናዬ በዳሶ ወራሽ አቶ አሸናፊ ረታ በሰበር ችሎት ቀርበው ችሎቱ መዝገቡን መርምሮ የሰጠው ፍርድ እንደሚያስረዳው ቀድም ሲል በመ/ቁ.34/211 በቀን 20/05/2007 ዓም የተሰጠውን ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 358 መሰረት በመቃወም ያቀረቡትን አቤቱታ የስር ፍርድ ቤቶች መቃወሚያው ውሳኔው ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ ነው በማለት በብይን ውድቅ ማድረጋቸውን ያሳያል። በሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ በመቃወም ለማስለወጥ ሲሆን አመልካቾች ሐምሌ 23 ቀን 2008 ዓ.ም በፃፉት አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ብይን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካቾች በስር በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ. 358 ላቀረቡት አቤቱታ ንብረቱ በአመልካቾች እጅ እያለና ፍርድ ሳይፈፀም እንደተፈፀመ ተደርጎ በአግባቡም ሳይጣራ በተፈፀመ ፍርድ መቃወሚያ ሊያቀርቡ አይችሉም ተብሎ አቤቱታቸው ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በመደረጉ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት በታዘዘው መሰረት 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች መጋቢት 7 ቀን 2009 ዓ.ም የተፃፈ የየራሳቸው መልስ ማቅረባቸውን ሰነዱ ያሳያል፡፡

1ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆናቸው በመገለጹ ወራሾች እንዲቀርቡ በጋዜጣና በመኖሪያ አድራሻቸው ጥሪ ቢደረግም ያልቀረቡ ስለሆነ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል። አመልካቾች 2ኛ እና 4ኛ ተጠሪዎች የሰጡት መልስ ላይ የመልስ መልስ የአመልካቾች ጠበቃ አልሰጥበትም በማለታቸው የቀረበ የመልስ መልስ የለም። የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን እኛም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን ለክርክሩ ከተያዘው ጭብጥ አንፃር ችሎቱ መርምሯል። በምርመራው መቃወሚያ የቀረበበት ፍርዱ ከተፈፀመ በኋላ የቀረበ ነው በማለት የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾችን መቃወሚያ አቤቱታ ውድቅ ያደረጉት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ ችሎቱ ይዞ ውሳኔ አሳልፏል። ውሳኔው በመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 34211 ግንቦት 2008 ዓ.ም የተሰጥቶ በፌደራል ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 180089 ሐምሌ 4 ቀን 2008 ዓ.ም በትዕዛዝ ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት መሻሩንና የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ለክርክር መነሻ የሆነው ቤት በውሳኔው መሰረት ወደ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ የተላለፈ መሆኑን አለመሆኑን በተጨባጭ ቤቱ በማን እጅ እንደሚገኝ በትክክል ውሳኔው የተፈጸመ መሆኑ አለመሆኑን አጣርቶ ተገቢው ውሳኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ.341 መሰረት መዝገቡ መመለሱን ያስረዳል።

በመጨረሻም በክፍል ሁለት በሚኖረን ዝግጅት የሕገ መንግስት አጣሪ ጉባኤን መልስ እና ከሰነዶች የምናገኛቸውን ማስረጃዎች ይዘን እንቀርባለን። እስከዚያው ቸር እንሰንብት።

# ነፃ ሃሳብ

# ለፅኑ ሀገረ መንግስት ግንባታ ብሔራዊ ጥቅምን ማስቀደም ያስፈልጋል

**መክሊት ወንድወሰን**

ውሉን መለየት በሚያስቸግር፣ እርስ በርስ በተሳሰረ እና ውስብስብ በሆነ ዓለም ውስጥ የግለሰብ እና የቡድን መብቶችን ከብሔራዊ ጥቅም ጋር አስታርቆ ለመሄድ የሚደረገው እንቅስቃሴ የፖለቲከኞችን የመምራት ችሎታ ከመፈታተኑም በላይ የርዕዮተ ዓለም ልዩነት በመፍጠር የክርክር እና የንትርክ ምንጭ ከሆነ ሰነባብቷል።

የዚህ ጽሁፍ ጥቅል ሃሳብ ከግል ጥቅም ይልቅ ብሄራዊ ጥቅም መቅደም አለበት የሚለውን ለማመላከት እንጂ ለበርካታ ጊዜያት ፖለቲከኞቻችን ጋግረው ያነኮሩትን እና አኝከው የተፉትን የግል እና የቡድን መብት ላይ ማብራሪያ ለመስጠት አይደለም። በእርግጥ ከግል ጥቅም ይልቅ ብሄራዊ ጥቅም መቅደም አለበት የሚለውም ሃሳብ አዲስ አይደለም፤ ለፖለቲካዊ ቲዎሪ እና ለመንግስት ስራ ምሶሶ ሆኖ የቆየ አመለካከት ነው።

እንደ ፕላቶ እና አርስቶትል እስከ ሆብስ እና ሩሶ ያሉ ዘመናዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ አመንጪ ፈላስፋዎች “የሃገር ጥቅም ከግለሰብ ወይም ከቡድን ጥቅም በላይ ነው” የሚለውን አስተሳሰብ የአንድ ሀገረ መንግስት ምሰሶ ወይም ማዕከላዊ መርህ መሆኑን አስቀምጠዋል። ከዚህ አመለካከት በስተጀርባ ያለው ምክንያት ግልጽና ቀጥተኛ ነው።

ብሔሮች የግለሰቦች ድምር ብቻ ሳይሆኑ የራሳቸው ግዴታዎች፣ የደህንነት መስፈርቶች እና የረጅም ጊዜ የእድገት ፍላጎቶች ያሏቸው ውስብስብ የማኅበረ ሰብ ስብስቦች መሆናቸውን ያመላክታል። በመሆኑም በየጊዜው ዓለምን እየፈተኑ ባሉት እንደ አየር ንብረት ለውጥ፣ ዓለም አቀፍ የጤና ቀውሶች እና መሰል ችግሮችን ለመቀልበስ በሚደረግ ትግል ውስጥ ሀገራት ከጠባብ ግለሰባዊ ጉዳዮች ይልቅ የጋራ ጥቅምን የማስቀደም አስፈላጊነት ከመቼውም ጊዜ በላይ የተገለጠላቸው ይመስላል።

አንድ ሀገር የውጭ ወታደራዊ ወረራ፣ የሽብርተኝነት ችግር ወይም ሌሎች የሀገርን ሉአላዊነት የሚጋፋ ችግሮች ሲፈጠሩ ሀገርን ማዳን ተግባር የቅድሚያ ቅድሚያ ይሰጠዋል። በዚህ ጊዜ ከግለሰብ እና ከቡድን መብቶች ይልቅ ብሄራዊ ጥቅምን ማስከበር የግድ ነው። እንዲህ ያሉ አጋጣሚዎች ሲፈጠሩም መንግስታት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃሉ። የአደጋ ጊዜ ኃይሎችን እስከመጥራት ይደርሳሉ።

ለምሳሌም እ.አ.አ 2020-2022 የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ሲከሰት በርካታ የዓለም ሀገራት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጆችን በማወጅ የግለሰቦችን እና ቡድን መብቶችን በእጅጉ የሚገፉ ጥብቅ ትዛዞችን ሲያስተላልፉ አይተናል። የእንቅስቃሴ ገደብ፤ ጭንብል የማጥለቅ እና ሌሎችም በርካታ ትዛዛት ተላልፈዋል። እነዚህ ትዛዞች “የሕዝቡን መብት የሚጥሱ” ቢሆንም እንኳን የሀገርን ደህንነት ለመጠበቅ የተደረጉ መሆናቸውን መገንዘብ ያስፈልጋል።

በተመሳሳይም ኢኮኖሚያዊ ቀውስ ወይም የተፈጥሮ አደጋዎች በሚከሰቱበት ጊዜ መንግስታት ከግለሰባዊ ፍላጎቶች ይልቅ ብሄራዊ መረጋጋትን እና ማገገምን የሚያስቀድሙ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ሊገደዱ ይችላሉ።

የብሔራዊ ጥቅም ቀዳሚነት በውጭ ፖሊሲያችን እና በዓለም አቀፍ ግንኙነቶች መስኩም በግልጽ ተመላክቷል። የአንድ አገር ስትራቴጂካዊ አቋም ወይም ዓለም አቀፋዊ ተፅዕኖ አደጋ ላይ ሲወድቅ መሪዎች ለብሔራዊ ጥቅም ሲሉ የግለሰብ ምርጫዎችን የሚሰዋ ከባድ ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ሊጠየቁ ይችላሉ።

ይህ ሲባል የብሔራዊ ጥቅሞች የግለሰብ እና የቡድን መብቶችን መድፈቅ አለባቸው፤ የግለሰብ ፍላጎቶች አስፈላጊ አይደሉም ወይም መንግስታት የግለሰብ ነጻነቶችን እንደፈለጉ መሻር እና መደፍጠጥ ይችላሉ ለማለት አይደለም። ይልቁንም ቀጣይነት ያለው እድገትና ለማምጣት አጠቃላይ የሀገር ደህንነት ለማረጋገጥ የብሔራዊ ጥቅሞች ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ለማስገንዘብ እና የብሔራዊ ጥቅሞች ከግለሰብ እና ከቡድን መብቶች ጋር ተጣጥመው፤ ሚዛኑን ጠብቀው መሄድ እንዳለባቸው ለማመላከት ነው።

> ብሄራዊ ጥቅም ከግል ጥቅም ለጽኑ ሀገረ መንግስት ግንባታ የሚኖረውን ፋይዳ በታሪክ መነጽር ማየት ይቻላል። የጋራ ጥቅም ለጠባብ የግልም ሆነ የቡድን አጀንዳዎች ሲታዘዝ ሊያደርሱ የሚችሉ አስከፊ መዘዞችን ከታሪክ ማየት ይቻላል

ብሔራዊ ጥቅምን ማስቀደም ከግለሰብ ደኅንነት ጋር የሚቃረን ሳይሆን፣ የሀገርን ደህንንት እና እድገት ዕውን ለማድረግ የሚከናወን ተግባር መሆን ይኖርበታል። የሀገሪቱን የረዥም ጊዜ የዕድገትና የልማት እቅዶች ለማሳካት ለግለሰቦች እድገት ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር፣ ዜጎች ጥራት ያለው ትምህርት፣ ጤና አጠባበቅ፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድሎች እና ምኞቶቻቸውን የሚያራምዱበት ደህንነቱ የተጠበቀ አካባቢን ለመፍጠር የብሔራዊ ጥቅሞችን ከግለሰብ እና ከቡድን መብቶች ጋር ተጣጥመው ሚዛኑን ጠብቀው መሄድ አለባቸው።

በእርግጥ በግለሰብ እና በብሔራዊ ጥቅም መካከል ያለው ትክክለኛ ሚዛን እንደየሀገሩ ልዩ ታሪካዊ፣ ባህላዊ እና ፖለቲካዊ ሁኔታ ይለያያል። ለሁሉም የሚስማማ መፍትሄ የለም። የፖሊሲ አውጪዎችም ተግዳሮት ይህንን ስስ ኩነት ሚዛናዊነት ያለማቋረጥ በመዳሰስ ለሚከሰቱ አደጋዎች እና እድሎች የግለሰብን መብትና ነፃነት በሚያስጠብቅ መልኩ ምላሽ በመስጠት የጋራ ጥቅሙንም ማስጠበቅ ነው።

ብሄራዊ ጥቅም ከግል ጥቅም ለጽኑ ሀገረ መንግስት ግንባታ የሚኖረውን ፋይዳ በታሪክ መነጽር ማየት ይቻላል። የጋራ ጥቅም ለጠባብ የግልም ሆነ የቡድን አጀንዳዎች ሲታዘዝ ሊያደርሱ የሚችሉ አስከፊ መዘዞችን ከታሪክ ማየት ይቻላል። ለብሄራዊ ጥቅም ቅድሚያ ሳይሰጥ ሲቀር ወይም የግለሰብና የቡድኖች ጥቅምን እና ፍላጎት ሲቀድም በመንግስታት ላይ የተከሰቱ ታሪኮችን ማንሳት እንችላለን፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ የሶቪየት ህብረት መበተን ምክንያቶቹን ማየት ተገቢ ነው። በታሪክ ውስጥ በርካታ የተበተኑ አገሮች ተመሳሳይ ዳይናሚክሶች የታዩባቸው ናቸው። ብሔራዊ ጥቅምን ለግለሰብ፣ ለቡድን ወይም ለርዕዮተ ዓለማዊ አጀንዳዎች መተው (ማመቻመች) የማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ መዋቅሮች እንዲወድቁ አድርጓል።

በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የነበረውን የዌይማር ጀርመንን ሁኔታ እንመልከት። ከአንደኛው የዓለም ጦርነት ማግስት፣ አዲስ የተመሰረተችው የዌይማር ሪፐብሊክ ከጦርነት እና ኢኮኖሚያዊ አለመረጋጋት እስከ ጥልቅ የፖለቲካ ክፍፍል እና የሀገር ቂም ስሜት የጎለበተበት ፈተናዎች አጋጥመዋታል። የዌይማር መንግስት ሀገሪቱን በአንድ የጋራ ሀገራዊ የመታደስ ራዕይ ላይ ከማስተሳሰር ይልቅ በእርስበርስ ሽኩቻ፣ የአስተሳሰብ ጦርነት እና ጠባብ ወገናዊ ጥቅምን በማሳደድ ሽባ አድርገዋታል።

ይህ ከግለሰብ ወይም ከቡድን አጀንዳ ይልቅ ብሔራዊ ጥቅምንና ፍላጎትን ማስቀደም አለመቻል ለአዶልፍ ሂትለር እና ለናዚ ፓርቲ መነሳት መንገዱን ጠርጓል። የዚህ ብሔራዊ ውህደት መፈራረስ ያስከተለው መዘዝ አስከፊ ነበር፣ ሃገራትን ወደ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት መርቷል፣ እልቂት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል በተጨማሪም ጀርመን ራሷ ለአደጋ ዳርጓታል።

በቅርቡ፣ እ.አ.አ በ2010ዎቹ መጀመሪያ ላይ የተነሳው የአረብ ሕዝባዊ አመጽ ሌላኛው ማሳያ ነው። በበርካታ የመካከለኛው ምስራቅ እና የሰሜን አፍሪካ ሀገራት ህዝባዊ ተቃውሞው መጀመሪያ ላይ የተቀሰቀሰው በኢኮኖሚ እኩልነት፣ በፖለቲካ ጭቆና እና መንግስት ለሕዝቡ ፍላጎት ምላሽ አለመስጠቱ እንደ ምክንያትነት የሚነሳ ነው። ይሁን እንጂ ሁከቱ እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር ትኩረቱ በስርዓት አገራዊ ችግሮችን ከመፍታት ወደ ግለሰባዊ ወይም ቡድናዊ ጥቅም ማስከበር፣ የአክራሪነት እንቅስቃሴዎችን ማባባስና ቀጠናውን ረዘም ላለ ጊዜ የእርስ በርስ ጦርነቶች መከተት መጨረሻው ሆነ።

እንደ ሶሪያ፣ ሊቢያና የመን ባሉ አገሮች የግለሰብና ብሔራዊ ጥቅምን ማስታረቅ ባለመቻሉ ሥራ ላይ ያሉ የመንግሥት ተቋማት መውደቅ፣ የማኅበራዊ ትስስር መሸርሸር፣ በአማፂ ቡድኖች፣ በጦር አበጋዞች የተሞሉ የሥልጣን ክፍፍሎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆኗል። ይሄውም በሚሊዮኖች የሚቆጠሩት እንዲፈናቀሉ፣ ለቁጥር የሚታክቱት ሕይወታቸው እንዲጠፋ፤ የመረጋጋት እና የማደግ ዕድሎችም በእጅጉ እንዲወድቁ አድርጓል።

እነዚህ የታሪክ ምሳሌዎች ከግለሰብ ወይም ከቡድን አጀንዳዎች ይልቅ ብሄራዊ ጥቅም ካልቀደመ ሊከተል የሚችለውን አስከፊ መዘዝ ያሳያሉ። በእያንዳንዱ ጉዳይ ላይ የጋራ ጥቅምን ለጠባብ የግል ፍላጎት ወይም ለርዕዮተ ዓለም መተው፤ የአገሪቱን ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ገጽታ ፈታኝ አድርጎ፤ በሕዝብና በሰፊው ጂኦፖለቲካዊ ገጽታ ላይ አስከፊ መዘዝ አስከትሏል።

ከታሪክ እንደሚያስረዳን የብሔራዊ ጥቅም ቀዳሚነት ረቂቅ መርህ ብቻ ሳይሆን፤ ለማንኛውም ማህበረሰብ የረዥም ጊዜ መረጋጋት፣ ደህንነት እና ብልጽግና ሊያመጣ የሚችል ቅድመ ሁኔታ ነው። በግለሰባዊ እና በጋራ ደህንነት መካከል ያለውን ውስጣዊ ጥገኝነት በመገንዘብ እና ከግለሰብ ወይም ከጥቅማጥቅሞች ይልቅ የጋራ ጥቅም በማስቀደም የሚያጋጥሙ ፈተናዎች ለመቋቋም የሚያስችል ጠንካራና ፍትሃዊ ማህበረሰብን መገንባት ያስፈልጋል፡፡

ሃሳቤንም ስጠቀልል ለማናችንም የሚበጀን ለብሔራዊ ጥቅም መስራትና በዛ ውስጥ የሚገቡንን ጥቅሞችና መብቶች ለማግኘት መጣር ነው። “እኔ እና ለእኔ” የሚሉ አመለካከቶች ሌሎችን ለበቀል እና ለጥላቻ የሚዳርግ ነው። ከተቻለ ከእኔ ይልቅ ለወንድሜ ይገባዋል! በሚል መተሳሰብ መኖር አስፈላጊ ነው። ፍትሃዊነት እና እኩልነትን (equity and equality) አስታርቆ መኖር የግድ ነው፡፡

ያንን ማድረግ ካልተቻለ እና “እኔ ብቻ ልክ ነኝ”፤ “ለኔ ብቻ ይገባል”፤ “እኔ ብቻ አውቅላችኋለሁ”፤ እጅ አውጥቶ ላልመረጣቸው ብሔር “ነጻ አወጣዋለሁ” ወይም ለምንና ለማን እንደሚታገል ሳያውቅ የሰው መብት እየነጠቀ “መብቱን አስከብርለታለሁ” የሚሉ ግለሰባዊ እና ቡድናዊ እሳቤዎች ሀገርን ሊበትኑ ይችላል። ስለዚህ ወገኔ! የሰውን መብትና ጥቅምን በማክበር የራስን መብትና ጥቅም ማስከበር ይቻላል መልእክቴ ነው።

# ፍትሐዊ የንግድ

## ስርዓትን ለማስፈን ያለመው መመሪያ

**ፍሕይወት አወቀ**

የንግድ ሥራ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ ዘመናትን ያስቆጠረ የኢኮኖሚ ማዕከል ነው። ያም ቢሆን ታዲያ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የንግድ ስርዓትን በአግባቡ የሚመራ ወጥ የሆነ የንግድ ፖሊሲ አልነበረም። በመሆኑም በፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አፈፃጸም እና በንግድ ዘርፉ ላይ ያሉ የንግድ እድሎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ስታንዳርዶች በተመለከተ የአሰራር ወጥነት ችግሮች ሲስተዋሉ ቆይተዋል። በአገሪቱ ሕገወጥ ንግድ መስፋፋቱም በዚሁ ምክንያት እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ።

በአገሪቱ ያለው የንግድ ስርዓት ጤናማ፣ ዘመናዊ፣ የተቀላጠፈና ሕግና ስርዓትን የተከተለ፤ ሸማቹን፣ ነጋዴውን፣ መንግሥትንና አጠቃላይ የንግዱን ማኅብረሰብ ተጠቃሚ ለማድረግም መንግሥት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ መቆየቱ አይዘነጋም። ከሚደረጉ ጥረቶች መካከልም በአሁን ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ እየገባ ያለው አዲስ የንግድ መመሪያ አንዱ ነው። መመሪያው በከተማዋ ጤናማ የሆነ የንግድ ስርዓትን በማስፈን ሸማቹን፣ ነጋዴውንና አጠቃላይ የንግዱን ዘርፍ ካላስፈላጊ ወከባና እንግልት የሚታደግ እንደሆነ ታምኗል፡፡

አዲሱና ወደ ሥራ የገባው መመሪያ ‹‹በመንደር የንግድ ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 159/2016 ዓ.ም›› ሲሆን፤ ቢሮው ከሰሞኑ በመመሪያው አተገባበር ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት አካሂዷል። የመመሪያው ዋና ዓላማ ከተማዋን ወደ ዘመናዊ የንግድ ስርዓት ውስጥ በማስገባት የተሻለ የንግድ እንቅስቃሴ እንዲኖር ማድረግ የሚል እንደሆነ የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ ኃላፊ አቶ ቢንያም ምክሩ ተናግረዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የአዲስ አበባ ከተማ ንግድ ቢሮ የተሰጠውን ኃላፊነት እየተወጣ ሲሆን፤ አንደኛ ፍትሃዊ የሆነ የንግድ ስርዓት በከተማዋ ለማስፈን፤ በየአካባቢው ያለውን የንግዱ ማኅበረሰብ የንግድ ሥራውን በሚሰራበት ጊዜ በተረጋጋና ከወከባ ነጻ በሆነ መንገድ ሥራውን በአግባቡ ማከናወን እንዲችል፣ እንዲሁም መንግሥት ያስቀመጠውን የንግድ ስርዓት የሚተላለፉ ነጋዴዎችን ወደ ስርዓት ማስገባት በመሆኑ ይህን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችል መመሪያ አዘጋጅቷል፡፡

መመሪያው ‹‹በመንደር የንግድ ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 159/2016 ዓ.ም›› ሲሆን መመሪያውን ወደ ሥራ ከመግባቱ አስቀድሞ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን ተናግረዋል። በመሆኑም አሁን ላይ መመሪያው ወደ ተግባር እየገባ ይገኛል። ያም ቢሆን ታድያ አሁንም የግንዛቤ የማስጨበጫ ስራው ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት በመሆኑ በቢሮው፣ በክፍለከተሞችና በወረዳዎች አማካኝነት ሥራው ተጠናክሮ ይቀጥላል በማለት አስረድተዋል፡፡

በተለይም በንግድ ቢሮ፣ በክፍለከተማና በወረዳ ደረጃ መሰራት ያለበት ሥራ ተጠናክሮ መቀጠልና ጤናማ የሆነ የንግድ ስርዓት በከተማዋ መስፈን እንዳለበት ነው። በዋናነት ሕግና ስርዓትን አክብረው የሚሰሩ ነጋዴዎች መብትና ግዴታቸው ምን እንደሆነና እንዲሁም ሕግና ስርዓትን ሳይጠብቁና ያለ ንግድ ፈቃድ የሚሰሩ ነጋዴዎች ደግሞ ምን አይነት እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚችል ግልጽ መረጃ በመያዝ ጥብቅ የሆነ ቁጥጥር ማድረግና ወደ ንግድ ስርዓቱ እንዲገቡ መሥራት ከአመራሩ ይጠበቃል። በተለይም የወረዳ አመራሮችና ባለሙያዎች ጥብቅ ቁጥጥር አድርገው የሚሠሩ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በ2017 በጀት ዓመት 230 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ ያቀደ መሆኑን ያነሱት አቶ ቢንያም፤ ይህን ዕቅድ ለማሳካት ከንግዱ ዘርፍ ብዙ የሚጠበቅና የተሰጠው ኃላፊነትም ትልቅ እንደሆነ ነው ያስረዱት። እሳቸው እንዳሉት ወደ ንግድ ስርዓቱ ያልገቡ ነጋዴዎች ላይ ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ይህን ኃላፊነት መወጣት ይቻላል፡፡

**ሕግና ስርዓትን አክብረው የሚሰሩ ነጋዴዎች መብትና ግዴታቸው ምን እንደሆነና እንዲሁም ሕግና ስርዓትን ሳይጠብቁና ያለ ንግድ ፈቃድ የሚሰሩ ነጋዴዎች ደግሞ ምን አይነት እርምጃ ሊወሰድባቸው እንደሚችል ግልጽ መረጃ በመያዝ ጥብቅ የሆነ ቁጥጥር ማድረግና ወደ ንግድ ስርዓቱ እንዲገቡ መሥራት ከአመራሩ ይጠበቃል**

ስለዚህ በከተማዋ በየትኛውም መንደርና ወረዳ ላይ ያለንግድ ፈቃድ የሚሰራ አንድም ነጋዴ እንዳይኖር የማድረግ ኃላፊነት የወረዳው መዋቅር በመሆኑ ወረዳው እዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ የሚሰራ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል። ከዚህ ቀደም ያለንግድ ፈቃድ ሲሰሩ የነበሩ ነጋዴዎች በሚገኙበት ጊዜ ንግድ ፈቃድ እንዲያወጡ የማድረግ ሥራ ሲሰራ መቆየቱን ያስታወሱት አቶ ቢንያም፣ ከዚህ በኋላ ግን ተደጋጋሚ የማስገንዘብ ሥራ ሲሰራ የቆየ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ማንኛውም ነጋዴ ያለንግድ ፈቃድ ሲሰራ ለቆየባቸው ጊዜ ሁሉ አስፈላጊውን ቅጣት ይቀጣል ነው ያሉት።

አያይዘውም ቢሮው በነቃ ጊዜ በሕጋዊ መንገድ የሚነግድና ባልተደረሰበት ጊዜ ደግሞ በሕገወጥ መንገድ የሚነግድ ነጋዴ በየትኛውም አካባቢ መኖር የለበትም ብለዋል። ስለሆነም ሁሉም ነጋዴ እስከሰራ ድረስ የመንግሥትን ሕግ አክብሮ ንግድ ፈቃድ አውጥቶ ለመንግሥት የሚገባውን ግብር እየገበረ መነገድ እንደሚገባው ማስገንዘብ ተገቢና የግድ መሆኑን ገልጸው፤ ለዚህም የወረዳ መዋቅር አንዱና ትልቁን ኃላፊነት የሚወስድ አካል በመሆኑ እዚህ ላይ ትኩረት አድርጎ እንዲሰራ አሳስበዋል።

ሌላው በንግድ ስርዓት ውስጥ ገብተው ንግድ ፈቃድ አውጥተው ለሚሰሩ ነጋዴዎችም እንዲሁ ወቅታዊ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን፤ በተለይም ወቅቱን ጠብቀው ንግድ ፈቃድ የማያድሱ ነጋዴዎች በወቅቱ ንግድ ፈቃዳቸውን እንዲያድሱ የማድረግ ኃላፊነት ይወጣል። ከእነዚህ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ውጭ ያሉ የተለያዩ ጥፋቶችን ነጋዴው ሲፈጽም ለሚቀጥለው ዕርከን መረጃዎችን በማቅረብ በከተማ ደረጃ እርምጃዎቹ የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

በከተማዋ በተደረገው ጥናት መሰረት በርካታ ነጋዴዎች ንግድ ፈቃድ ሳያወጡ በየወረዳው የንግድ ሥራ እንደሚሰሩ የጠቀሱት አቶ ቢንያም፤ ወረዳው በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት ትኩረት አድርጎ ከሠራ የንግድ ሥርዓቱን ስርዓት በማስያዝና የከተማውን ገቢ በመጨመር ረገድ ጉልህ አስተዋጽኦ እንዳለው ተናግረዋል። የመመሪያው ተግባራዊነት በየመንደሩ ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ሳይኖራቸው የንግድ ሥራ የሚሰሩ ነጋዴዎች ላይ እርምጃ ለመውሰድ፣ በተቃራኒው ደግም ህጋዊ ሆነው የሚሰሩ ነጋዴዎች ሥራቸውን በአግባቡ እንዲሰሩ ለማስቻል ትልቅ አቅም የሚፈጥር በመሆኑ ለንግዱ ዘርፍ ትልቅ አበርክቶ እንዳለውም ተናግረዋል።

‹‹ከተማዋ በቀጣይ ለማግኘት ያቀደችውን ገቢ ማሳካት የምትችለው መመሪያውን በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲቻል ነው›› ያሉት አቶ ቢንያም፤ ለዚህም ቢሮውን ጨምሮ ክፍለከተሞች ትልቅ ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም መመሪያውን በአግባቡ ተግባራዊ በማድረግና የሚፈለገውን ውጤት ለማምጣት ወረዳዎች ትልቁን ድርሻ ይወስዳሉ ብለዋል፡፡

የአዲስ አበባ ነጋዴዎች ማህበር ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ዘህራ መሀመድ በበኩላቸው በመንደር የንግድ ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 159/2016 ዓ.ም መመሪያ በተለይም ለንግዱ ማኅበረሰብ ምቹና ቀልጣፋ ከመሆኑም በላይ ትላልቅ ችግሮችን የሚያስቀርና ወደ ሥራ የሚያስገባ መመሪያ እንደሆነ ያላቸውን ዕምነት ገልጸዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ በአሁን ወቅት ሕገወጥ ንግድ እጅግ የተንሰራፋበትና በተቃራኒው ደግሞ ሕጋዊ ነጋዴ የተበደለበትና የተጨቆነበት የንግድ ስርዓት ነበር ያለው።

ይሁንና ይህ ወደ ሥራ እየገባ ያለው አዲስ መመሪያ በንግዱ ዘርፍ እየተስተዋሉ የነበሩ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ማቃለል የሚችል ነው። ለዚህም ዛሬ ላይ ከወረዳ ጀምሮ እየተሰሩ ያሉ የጋራ ሥራዎች ማሳያዎች ናቸው ብለዋል። ፖሊሲና ስትራቴጂ በማውጣት ሕግ አውጭውና ሕግ አስፈጻሚው አካል በጋራ በመሆን የሚሰሩት ሥራ ነው። በመሆኑም ሕገወጥና ሕጋዊ የሆነውን ነጋዴ በቀላሉ መለየት የሚያስችል የንግድ ቁጥጥር ስርዓት እንደሆነና ለንግድ ስርዓቱ ጤናማነት ትልቅ አበርክቶ እንዳለው ተናግረዋል፡፡

በተለይም ከታች ባለው የንግዱ ማህበረሰብ በንግድ ቁጥጥሩ ላይ ፍትሐዊ ያልሆኑና ጉራማይሌ የሆኑ አሰራሮች ይስተዋሉ እንደነበር ያነሱት ወይዘሮ ዘሀራ፤ ሕግ አስፈጻሚው ደስ ባለው ሰዓት ተነስቶ የንግድ ድርጅቶችን የሚያሽግበትና ለሙስና የሚጋበዝበት አሰራር እንደነበረም አልሸሸጉም። ሌላው ሕጋዊ ነጋዴው ሕገወጡን በመመልከት ወደ ሕገወጥ መንገድ እየወጣ የነበረና ሕገወጥ ንግድ በእጅጉ እየተንሰራፋ ያለበት ጊዜ መሆኑን አስታውሰዋል፡፡

በመንደር የንግድ ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 159/2016 ዓ.ም ሕገወጡን ነጋዴ ወደ ሕጋዊ መስመር ለማስገባት፤ ሕጋዊ ነጋዴውን ደግሞ ደግፎ ለመስራት የሚያስችል ምቹ ሜዳ መሆኑን የገለጹት ወይዘሮ ዘሀራ፤ መመሪያው በተለይም በመሰረታዊ የፍጆታ ዕቃዎች ላይ ባዕድ ነገሮችን መቀላቀል እና ሌሎች ጥፋቶችም በዝርዝር የተቀመጡና የሚያስቀጡ እንዲሁም ስርዓት ተበጅቶላቸው የተቀመጡ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በንግዱ ማኅበረሰብ በርካታ ችግሮች ስለመኖራቸው ጠቅሰው፤ ነጋዴውን ጨምሮ ኅብረተሰቡንና መንግሥትን ጭምር የሚያውኩ በርካታ ሕገወጥ ነጋዴዎች መኖራቸውን ተናግረዋል። ይሁንና መመሪያው እነዚህን ነጋዴዎች ጭምር ወደ ሕጋዊ መንገድ ለመመለስ የሚያስችል ዕድል ያለው መሆኑን አመላክተዋል።

መመሪያውን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች እንዳሉ የገለጹት ወይዘሮ ዘሀራ፤ ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችን ለመፍታትም የተለያዩ አማራጮች እንዳሉ ሲያስረዱ፤ በተለይም የንግዱ ማህበረሰብ፣ ንግድ ቢሮ፣ ገቢዎችና ፖሊስ በጋራ ተቀናጅቶ ታች ድረስ ወርዶ መስራት እንዳለበትና ከዚህ ቀደምም መሰል ሥራዎች ሲሰሩ እንደነበር አስታውሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ እነዚህ አካላት ከዚህ ቀደም መርካቶ አካባቢ ተቀናጅተው በሰሩት ሥራ ከ24 ሺ በላይ የሚሆኑ ንግድ ፈቃድ ሳያወጣ የሚነግዱ ሕገወጥ ነጋዴዎችን በመለየት ሕግና ስርዓት ውስጥ እንዲገቡ የማድረግ ሥራ መሥራት ተችሏል። አሁንም ቢሆን አዲሱን 159/2016 መመሪያ የተሻለና ቀጣይነት ያለው ሥራ መሥራት የሚያስችል እንደመሆኑ በከተማዋ ጤናማ፣ የተረጋጋና ፍትሐዊ የሆነ የንግድ ስርዓት እንዲፈጠር ያስችላል።

‹‹በመንደር የንግድ ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት መመሪያ ቁጥር 159/2016 ዓ.ም በዋናነት ሕጋዊ ነጋዴውን በእጅጉ የሚጠቅም ነው›› ያሉት ወይዘሮ ዘሀራ፤ ሕጋዊ ነጋዴው ግብር ከመገበር ጀምሮ የተለያዩ ወጪዎችን ተቋቁሞ ሲሰራ በተቃራኒው ሕገወጥ ነጋዴው የማይስተካከል ከሆነ ሕጋዊ ነጋዴው ወደ ሕገወጥ ንግድ የሚገባበት መንገድ ሰፊ መሆኑን አንስተው በዚህም በርካታ ችግሮች ተፈጥረው መመልከት እንደቻሉ ነው ያስረዱት። ስለዚህ ንግድ ቢሮ ከገቢዎች ጋር ተቀናጅቶ በመሥራት የንግድ ስርዓቱን የሚያስተጓጉሉ ችግሮችን ነቅሶ በማውጣት፤ ሕጋዊ ነጋዴውን መደገፍና ማበረታታት፤ እንዲሁም ሕገወጥ ነጋዴውን ወደ ሕጋዊ መስመር የማስገባት ትልቅ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን አመላክተዋል።

ነጋዴውና ሸማቹ አጠቃላይ የንግዱ ማኅበረሰብ መብትና ግዴታውን በአግባቡ እንዲያውቅና እንዲረዳ፤ የንግድ ሥርዓቱ የተረጋጋና ያለወከባ መስራት የሚችልበትን ዕድል መፍጠር እንዲያስችለው ታስቦና ታቅዶ የወጣው በመንደር የንግድ ቁጥጥር የአሰራር ስርዓት መመሪያ በተለይም በዚህ ሂደት ውስጥ ከቁጥጥር ጋር ተያይዘው የሚስተዋሉ ብልሹ አሰራሮችን ወጥ በሆነ የቁጥጥር ስርዓት ለማስኬድ እንደሆነም ተመላክቷል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የመንግሥት ሠራተኛ ለምን ይቀለድበታል?

**ዋስልኝ አየለ**

አንዳንድ ነገሮች አጀንዳ የሚሆኑት ሰዎች ያንን ነገር ትኩረት ሰጥተው ልብ ስለሚሉት ነው:: «ሰው የልቡን ሲነግሩት የኮረኮሩትን ያህል ይስቃል» እንደሚባለው አንድ ነገር በብዛት የሚሰራጨው የሰዎችን የውስጥ ስሜት ስለሚነካካ ነው፤ አለበለዚያ ማንም ልብ አይለውም::

ሰሞኑን ሪፖርተር ጋዜጣ ላይ የወጣው «ኑሮ የከበዳቸው የመንግሥት ሠራተኞች የምሳ ሰዓት በቤተ እምነቶች እያሳለፉ መሆኑ ተነገረ» የሚለው የዜና ርዕስ በማህበራዊ ገፆች በቀልድም በቁም ነገርም አጀንዳ ሆኖ ነበር:: የዜናውን ዝርዝር ስታዩት ግን አንድ የመንግሥት የሥራ ኃላፊ በረቂቅ አዋጁ ላይ የሰጡት አስተያየት ነው እንጂ በጥናት የተረጋገጠ አይደለም:: የመንግሥት ሠራተኞች ያላቸው የእረፍት ሰዓት በምሳ ሰዓት ስለሆነ ምናልባት በዚያ ሰዓት ወደ ቤተ እምነት ሲሄዱ አይተው ሊሆን ይችላል:: ምሳ አልያዛችሁምና ከቢሮ ውጡ የሚል የለም እኮ! እንዲያውም ሲባል የምንሰማው በአንዳንድ መስሪያ ቤቶች ቢሮ ውስጥ የምግብ ትርፍራፊ እንዳይኖር፣ የቢሮው ጠረን ምግብ ምግብ እንዳይል (የሥራ ቦታ ስለሆነ) የሚከለክሉ እንዳሉ ነው:: ምግብ ካልያዛችሁ ብሎ «ውጡ!» የሚል የለም::

እንዲያውም እኔ የማውቀው በተቃራኒው ነው:: ምሳ የሚቋጥሩ ሰዎች ባለትዳር የሆኑ እና ገንዘብ ለመቆጠብ የሚያደርጉት ነው ተብሎ ነው የሚቀለድ፤ ምሳ የማይዙት ደግሞ ላጤ የሆኑ እና ውጭ በየካፌውና በየሆቴሉ የሚመገቡ ተደርጎ ነው የሚታሰበው:: በመሰረቱ ሁለቱም ትክክል አይደለም:: ምሳ መቋጠርም ሆነ አለመቋጠር ከግል ፍላጎት ጋር የሚያያዝ እንጂ የኑሮ ደረጃ መለኪያ አይደለም፤ እንዲያውም ለጤና የሚሻለው የቤት ምግብ መያዝ ነው:: በቢሮ ውስጥ ባለው ልማድ ግን ምሳ ያልቋጠረ ሰው እንደ ልዩ ድሃ የሚታይ አይደለም ለማለት ነው::

ያም ሆነ ይህ ዋናው ጉዳይ ግን ይህ አይደለም:: የመንግሥት የሥራ ኃላፊው ይህን አስተያየት ቢሰጡም ባይሰጡም፣ ሪፖርተር ጋዜጣ ይህን ዜና ቢሰራውም ባይሰራውም፤ የመንግሥት ሠራተኞች የኑሮ ችግር አጀንዳ ነበር፤ መቀለጃ ነበር:: በወር ደሞዝ የሚኖር ሰው ምን ያህል ችግር ውስጥ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው:: የቤት ኪራይ ከተከራዩ የደሞዝ ጣሪያ በላይ እየሆነ መሆኑን ማንም ያውቃል::

ይህ አጀንዳ፤ አጀንዳ ከመሆኑ በፊትም በመንግሥት ሠራተኞች ላይ ይቀለዳል:: በፊልሞች፣ በመድረኮች፣ በመገናኛ ብዙኃን ከኑሮ ጋር በተያያዘ የሚሰሩ ቀልዶች ይዘታቸው የመንግሥት ሠራተኛን በችግረኛነት የሚስሉ ናቸው:: ይህ ለምን ሆነ? ለምን ድሮ የነበረው ክብር አሁን ጠፋ? ጉዳዩ በሠራተኛው ድህነት ብቻ ወይስ በሌላ?

የኑሮ ውድነቱ እንዳገር ስለሆነ ምንም ትዝብትም ሆነ አስተያየት አያስፈልገውምና እንለፈው:: የኑሮ ውድነቱ በየመገናኛ ብዙኃኑና በየመድረኩ አጀንዳ ስለሆነ ብዙ ተብሎበታል:: አንድ ግን ልብ ያልተባለ የሚመስለኝ ነገር አለ:: እዚህ ላይ ደፈር ብለን የመንግሥት ሠራተኛውን እና የራሱ የመንግሥትን ችግሮች ልንናገር ይገባል:: ማስመሰልና መደባበቅ ወደ ዕድገትና ሥልጣኔ አይወስድም::

የመንግሥት ሠራተኞች ሊሆኑ የሚገባውን ያህል የነቁ እና የሠለጠኑ አይደሉም:: አርዓያ መሆን ሲገባቸው መሆን አልቻሉም:: የድሮውን እናስታውስ:: ከአሥርት ዓመታት በፊት «የቢሮ ሠራተኛ» የሚለው ትርክት ትልቅ ክብር ያለው እና ብዙዎች የሚመኙት ነበር:: እንዲያውም የዚያ ልማድ ተፅዕኖ አድርጎባቸው ብዙ ወላጆች ልጆቻቸው የመንግሥት ሥራ ሲቀጠሩ እጅግ በጣም ደስ ይላቸዋል:: በገቢ የተሻለ ሌላ ሥራ ላይ ከሚሰማራ ይልቅ በገቢ አነስተኛ ሆኖ የመንግሥት ተቋም ውስጥ ሲቀጠር እንደ ልዩ ክብር ይታይ ነበር::

ይህ የሆነበት ምክንያት የመንግሥት ተቋም ሠራተኛ መሆን፤ የመማር፣ የመሰልጠን፣ የማወቅ፣ በአጠቃላይ ከሌሎች የተሻለ ሁሉን አዋቂ ተደርጎ ይወሰድ ስለነበር ነው:: እንኳን ሌላ ቀደም ባለው ጊዜ የግል ንጽህና ሳይቀር የሚኮረጀው ከመንግሥት ሠራተኛ ነበር:: አስተዋይነት፣ ጨዋነት፣ ግርማ ሞገስ፣ ስክነት የመሳሰሉት አሉ ተብሎ የሚጠበቀው ከመንግሥት ሠራተኛ ነበር:: እነዚህ ነገሮች ይኖሩታል ተብሎ የሚታመነው ደግሞ በምንም ሳይሆን የተማረ ስለሆነ ነው::

በአሁኑ ዘመን ግን ትምህርት ስለተስፋፋ አብዛኛው ዜጋ የተማረ ነው:: ወዲህ ደግሞ ቴክኖሎጂው ምቹ ስለሆነ ሁሉንም እኩል የማድረግ ዕድሉ ተፈጥሯል:: ይህ ጥሩ አጋጣሚ ነው፤ እንኳንም ሆነ የሚያሰኝ ነው::

ችግሩ ግን ወዲህ ነው! ደፈር ብለን እንናገር ከተባለ የመንግሥት ሠራተኛው ያለው ንቃት እና ብቃት ከነጋዴ እና ከገበሬ እያነሰ ነው:: ለሥልጣኔ የበለጠ አርዓያ መሆን ሲገባው የዝርክርክነትና የግዴለሽነት ማሳያ እየሆነ ነው:: አንድ የግል ንግድ ቤት ውስጥ የማይታይ ብልሹ ድርጊት የመንግሥት ተቋም ውስጥ ይታያል:: ለሁሉ ነገር ሞዴል መሆን ሲገባው ጭራሽ በተቃራኒው በግለሰቦች ቤትና ተቋም ውስጥ ባሉ ሥልጣኔዎች የተበለጠ ሆነ:: የሚታዩት ችግሮች ደግሞ የገንዘብ ሳይሆን የአስተሳሰብ ችግሮች ናቸው:: ከፍተኛ የሆነ ግዴለሽነት ስላለ ነው:: በዕውቀትና በአስተሳሰብ እየተበለጡ መጡ፤ እንዲያውም ይባስ ብሎ አዋቂና አስተዋይ የሆነ ሰው ሲያጋጥም የሚመከረው ምክር ከመንግሥት ቤት እንዲወጣ ነው::

በሕክምናው እና በትምህርቱ ዘርፍ ልብ በሉ! የተሻለ ዕውቀት ያለው «የግል ትምህርት ቤት ነው፣ የግል ሆስፒታል ነው» የሚለው ትርክት ስር እየሰደደ ነው:: ይህ ደግሞ አደገኛ ትርክት ነው:: የመንግሥትን ተቋማት እምነት እንዳይኖራቸው ያደርጋል:: ይህ ብቻ አይደለም፤ የልጆችንም ስነ ልቦና ይጎዳል:: ምኞታቸው የመንግሥት ተቋም ውስጥ ገብቶ አገር ማገልገል ሳይሆን ገንዘብ ነክ ነገር ብቻ እንዲሆን ያደርጋል::

ይህ ለምን ሆነ? ከተባለ ግን የመንግሥት በቂ ክትትል አለመኖርና ለጉዳዩ ትኩረት አለመስጠት ነው:: ከአካዳሚ የትምህርት ደረጃ ባሻገር የሠራተኞችን ስነ ምግባርና ሰብዓዊነት የመለየት አሰራር ስለሌለ ነው:: ቢሮ ውስጥ መጮህ፣ ንፅህናን አለመጠበቅ ጎልተው የሚታዩ ችግሮች ናቸው:: ቀላልና ተራ ችግሮች ቢመስሉም አለመሰልጠንን ያሳያሉ::

ወዲህ ደግሞ ከራሱ ከአመራሩ ጀምሮ በሙስና እና ብልሹ አሰራር የተተበተበ ስለሆነ ነው:: ከአንድ ቦታ በስርቆት የተባረረ አመራር ሌላ ቦታ በሌላ ኃላፊነት (ምናልባትም በተሻለ) ሊመደብ ስለሚችል ነው:: ይህ ለብዙ ዓመታት ሲወቀስ የቆየ ችግር ነበር:: ሥልጠና ሲሰጥ እንኳን ከመንግሥት ፖሊሲና ስትራቴዎጂዎች ጋር የተያያዘ ጉዳዮች ይበዙበታል:: መሰልጠንን፣ ሰብዓዊነት ቀረጻን፣ በአጠቃላይ ስነ ምግባር ተኮር የሆኑ ሥልጠናዎች አይሰጡም:: ሠራተኞች «ብቁ» የሚባሉትም ምናልባትም የማያረፍዱ ወይም ከሥራ የማይቀሩ በመሆናቸው እንጂ በጨዋነትና በስነ ምግባር ማበረታቻ ሲደረግ ብዙም አይታይም::

በመሰረቱ የመንግሥት ሠራተኛ ለእነዚህ ነገሮች ማበረታቻ የሚያስፈልገው መሆን አልበረበትም፤ አገር ሊቀይር አገር የተረከበ ዜጋ ነው:: በመንግሥት ተቋም ውስጥ ምናልባትም ከመጀመሪያ ዲግሪ በታች የትምህርት ደረጃ ብዙም የለም:: ከዩኒቨርሲቲ የተመረቁት አገር ሊረከቡ ቃለ መሃላ ፈጽመው ነው:: ስለዚህ የነቁ እና የበቁ መሆን አለባቸው::

በአጠቃላይ ግን ችግሩ ከራሱ ከሠራተኛውም ከመንግሥት አመራሮችም ሥር የሰደደ ነው:: በዚህ ሁኔታ ደግሞ የተለመደውን ትርክት መቀየር አንችልም፤ ስለዚህ ሁሉም በቆራጥነት መሥራት አለበት:: አዲስ የንቃትና የብቃት ባህል መገንባት አለበት:: የመንግሥት ሠራተኛው የድህነትና የኋላቀርነት መቀለጃ መሆን የለበትም! ለዚህ ደግሞ መፍትሔው «ለምን እንዲህ አሉኝ!» እያሉ መፎከር ሳይሆን ለመለወጥ መዘጋጀት ነው:: የንቃት እና የብቃት፣ የሥልጣኔ እና የሰብዓዊነት፣ የአስተዋይነትና የትህትና አርዓያዎች መሆን አለብን!

# ዓለም አቀፍ

## በሰው አእምሮ ውስጥ በሚቀበሩ ቺፕሶች ላይ ሁለተኛ ሙከራ ሊደረግ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የአሜሪካዊው ቢሊየነር ኢሎን መስክ የሆነው የባዮ ቴክኖሎጂ ኩባንያ ኒውራሊንክ ባለፈው ጥር ወር የመጀመሪያውን ችፕስ በሰው አእምሮ ውስጥ የቀበረ ሲሆን አሁን ደግሞ ለሁለተኛ ሙኩራ እየተዘጋጀ ነው።

የመስክ የባዮቴክ ኩባንያ የ30 ዓመት እድሜ ባለው ግለሰብ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ችፕስ የገጠመው ባለፈው ጥር ወር ነበር። የአነስተኛ ሳንቲም መጠን ያላትን ቺፕስ የሰው ልጅን እንቅስቃሴ ፍላጎት ከሚያዘው የአእምሮ ክፍል ላይ በቀዶ ጥገና እንድትቀመጥ ተደርጓል። ይህቺ ቺፕስ "የአእምሮን እንቅስቃሴ በመመዝገብ እና የእንቅስቃሴ ፍላጎትን ወደሚተረጉም መተግበሪያ ወይም አፕ" ለማስተላለፍ ጥቅም ላይ ውላለች።

ኒውራሊንክ ባለፈው ዓመት በሰጠው መግለጫ ፕሪሳይዝ ሮቦቲካሊ ኢምፕላንትልድ ብሬን ኮምፒውተር (ፒአርአይኤሜኢ) ፕሮግራም ዓላማ ሙሉ በሙሉ የሚቀበር እና ዋየርለስ ብሬን ኮምፒውተር በማልማት ሰዎች በማሰብ ብቻ የኮምፒውተር ከርሰር ወይም ኪቦርድ እንዲቆጣጠሩ ማስቻል እንደሆነ ገልጾ ነበር።


ይህ አይነስውራንን፣ ሰውነታቸው የማይታዘዝላቸውን እና የመሳሰሉ የአካል ጉዳት ያለባቸውን እንዲሁም ከመጠን ያለፈ ውፍረት፣ የአእምሮ ውስንነት፣ ድብርትና ስኪዞፈርኒያ አይነት በሽታዎች ያሉባቸውን ሰዎች ለማከም መንገድ የሚጠርግ ነው ተብሏል።

የአሜሪካ የምግብ እና የመድሃኒት አስተዳደር (ኤፍዳኤ) የመጀመሪያው የቺፕስ ቀበራ ወይም ቸፕስ ኢምላንቴሽን ያጸደቀው ባለፈው ግንቦት ወር ነበር።

ባለፈው ጥር ወር የቺፕስ ቀበራው ከተካሄደ ከበርካታ ሳምንታት በኋላ የተቀበረለት ሰው "ሙሉ በሙሉ ማገገሙንና ምንም ህመም እንደሌለበት" እንዲሁም የኮምፒውተር ማውዝን "በማሰብ ብቻ" በስክሪን ላይ ማንቀሳቀስ መቻሉን መስክ ሪፖርት ማድረጉ ይታወሳል።

ነገርግን ባለፈው ግንቦት ወር በአእምሮ ውስጥ የተቀበረች ቺፕስ ከቦታዋ በመንሸራተቷ ምክንያት ትንሽ ችግር አጋጥሞት እንደነበር አምኗል። ያም ሆኖ ኤፍዲኤ ሁለተኛው የቺፕስ መቅበር ሙከራ እንዲደረግ ፍቃድ መስጠቱን ዋል ስትሬት ባለፈው ወር ዘግቧል።

በዚህ ወር ይካሄዳል በተባለው ሁለተኛው ሙከራ፣ ቺፕሱ እንዳይንሸራተት ጠለቅ ብሎ ወደ አእምሮ ውስጥ እንዲቀበር ይደረጋል ተብሏል። ያም ሆኖ ኤፍዲኤ ሁለተኛው የቺፕስ መቅበር ሙከራ እንዲደረግ ፍቃድ መስጠቱን አል አይን ወር ዘግቧል።





## የሩሲያና የሰሜን ኮሪያ ግንኙነት እየተጠናከረ መጥቷል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የሩሲያና የሰሜን ኮሪያ ግንኙነት እየተጠናከረ መምጣቱን ተከትሎ የሩሲያው ፕሬዝዳንት ቭላድሚር ፑቲን ከ24 ዓመት በኋላ በሰሜን ኮሪያ ጉብኝት አድርገዋል።

ፕሬዝዳንቱ ከጉብኝታቸው አስቀድሞ በላኩት ደብዳቤ ሰሜን ኮሪያ ሞስኮ በዩክሬን የምታካሂደውን ጦርነት "በጽኑ መደገፏን" ማድነቃቸውን የሰሜን ኮሪያ ብሄራዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ ዘግቧል።

በዚህ ጉብኝታቸውም ከኪም ጋር በደህንነትና ሌሎች ጉዳዮች የትብብር ስምምነት እንደሚፈራረሙ ይጠበቃል ብሏል ክሬምሊን።

ሀገራቸው ከፒዮንግያንግ ጋር "ከምዕራባውያን ቁጥጥር ውጭ የሆነ" የንግድ እና ደህንነት ስርዓት እንደምትገነባ መናገራቸውንም ነው ዘገባው የጠቆመው።

በፒዮንግያንግ ከሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጀንግ ኡን ጋር የተገናኙት ፑቲን፤ ሰሜን ኮሪያ "የአሜሪካን ጫና፣ ማጭበርበርና ወታደራዊ ስጋት" ለመመከት የምታደርገውን ጥረት ሞስኮ እንደምትደግፍ መናገራቸውንም የሰሜን ኮሪያው ገዥ ፓርቲ ልሳን የሆነው ሮዶንግ ሲንሙን አስነብቧል።

የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን ባለፈው መስከረም ወር በሩሲያዋ ቮስቶችኒ ኮስሞድሮም ከፕሬዚዳንት ፑቲን ጋር መገናኘታቸው ይታወሳል።

ፑቲን ግን በሰሜን ኮሪያ ለመጨረሻ ጊዜ ጉብኝት ያደረጉት እ.አ.አ. በ2000 እንደነበር ሬውተርስ አስታውሷል። ኪም ባለፈው ሳምንት የሩሲያና የሰሜን ኮሪያ ግንኙነት "ማንም የማይበጥሰው" ደረጃ መድረሱን መናገራቸው አይዘነጋም።

አሜሪካ በበኩሏ የሀገሪቱ ትብብር እያደገ መሄድ እንደሚያሳስባት ገልጻለች። የሀገሪቱ ብሄራዊ የደህንነት ምክርቤት ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢ፤ "የሚያሳስበን የፑቲን ጉብኝት ሳይሆን የሀገራቱ ግንኙነት በየጊዜው እያደገ መሄዱ ነው" ብለዋል።

ዋይትሃውስ ሩሲያ በዩክሬን ጋር በገባችበት ጦርነት የፒዮንግያንግ የጦር መሳሪያዎች ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው፤ ሞስኮም ለሰሜን ኮሪያ የስፔስ ቴክኖሎጂ ድጋፍ እያደረገች ነው የሚሉ ክሶችን ሲያቀርብ መቆየቱ ይታወቃል።

ፑቲንም ሆነ ኪም የዋሽንግተንን ክስ ባይቀበሉትም ሁለቱ ሀገራት የምዕራባውያኑን ማዕቀብና ጫና በትብብር ለመፍታት የሚያስችል ግንኙነት በመመስረት ላይ ናቸው።

# ባለውለታዎቻችን

# ከባርነት ወደ ላቀ ምሁርነት

ክብረአብ በላቸው

ኢትዮጵያ፣ ደማቅ ታሪክ ያላቸው በርከት ያሉ ሰዎች አገር መሆንዋ የታወቀ ቢሆንም፤ ታሪካቸው በአግባቡ በወረቀት ላይ ተፅፎ የተመዘገበው የጥቂቶቹ ብቻ ነው። በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችና ባገኟቸው ዕድሎች በአገር ውስጥና በውጭ አገር ዕውቀት ለመቅሰምና የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት የቻሉ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን መኖራቸው የሚታወቅ ነው። እነኚህ ኢትዮጵያውያን ያገኙትን ዕውቀት ለወገኖቻቸው ለማድረስና አዳዲስ አሠራርንና አስተሳሰብን በሕዝባችን መካከል እንዲሰርጽ ለማድረግ ሲጥሩ ተስተውለዋል፤ መልካሙን ለማድረግ አብዝተው የደከሙና ሕይወታቸውን አሳልፈው እስከ መስጠት የደረሱ ፋና ወጊ ምሁራን እንደ ነበሩም ይታወቃል።

ሀገራቸውን ከውጭ ወራሪና ጠላት በመከላከል አኩሪ ታሪክ የሠሩ፣ የሕዝባቸውን ደኅንነትና አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ መሥዋዕትነት የከፈሉና አንፀባራቂ ታሪክ የሠሩ ጥቂቶች አልነበሩም። በደራሲነት፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በስፖርት፣ በታሪክ፣ በሳይንስና በእምነት አስተምህሮ፣ የኪነ ጥበብና የምርምር ሥራዎችም ኢትዮጵያን በዓለም የበለጠ እንድትታወቅ ያደረጉ ትናንትናም ዛሬም ደምቀው የሚታዩ ደማቅ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብዙዎች ናቸው። ከእነዚህ መካከል የኦሮሚኛ መፅሐፍ ቅዱስ ተርጓሚው ኦነሲሞስ ነሲብ አንዱ ናቸው።

ኦነሲሞስ፣ የተወለደው በ1848 ዓ.ም ኢሉባቦር 'ሁሩሙ' በምትባል መንደር ነበር። የልደት ስሙ 'ሂካ' (Hiikaa) ይባል ነበር። ስሙ በአፋን ኦሮሞ 'ፈቺ' የሚል ትርጉም ያለው ነው። ኦነሲሞስ፣ አባቱን ሞት የነጠቀው ገና የአራት ዓመት ህጻን ሳለ ነበር። ገና በለጋነት እድሜው ጋሻ ከለላ የሚሆነውን አባቱን ያጣው ሕጻኑ ኦነሲሞስ፣ በዘመኑ ተጧጡፎ ለነበረው ለባሪያ ፍንገላ ተጋለጠና በባሪያ ፈንጋዮች እጅ ወደቀ። ኦነሲሞስ በባሪያ ፈንጋዮች እጅ ከወደቀበት ጊዜ ጀምሮ የኖረው ለአስራ ሁለት ዓመታት ያህል እንደ ሸቀጥ ሲሸጥ ሲገዛ በመንከራተት ነው።

ከአስራ ሁለት ዓመታት የእንግልትና የባርነት ሕይወት በኋላ ኦነሲሞስ እድል ፊቷን አዞረችለት። ዋርነር ሙዚንገር (Werner Münzinger) የተባለ የስዊድን ሰው ኦነሲሞስን ገዝቶ ነጻ አውጥቶ ለስዊዲሽ ሚሲዮን አስረከበው። በዚህን ወቅት ነበር ሂካ ተብሎ በእናት አባቱ የወጣለት ስም ወደ ኦነሲሞስ ነሲብ የተቀየረበት አጋጣሚ የተፈጠረው።

ከሂካ ወደ ኦነሲሞስ ነሲብ የተደረገው የስም ለውጥ ውስጥ ሁለት ባለታሪኮች ይነሳሉ። አንደኛው ኦነሲሞስ ነሲብን በባርነት ያሳድር የነበረ ሰው ነው። ይህ ሰው ኦነሲሞስ ነሲብን በባርነት ካሳደሩት ሰዎች ሁሉ ደጉ እሱ ስለነበር 'ነሲብ' የሚለው ስም ከዚህ ሰው ስም እንደተወሰደ ነው ታሪክ የሚያስረዳው።

ሌላው የስሙ መነሻ 'ቅዱስ ' ኦነሲሞስ የተባለ የቅዱስ ጳውሎስ ደቀ መዝሙር የነበረ ሰው ነው። ይህ ሰው ልክ እንደ ሂካ ሁሉ ባሪያ የነበረና ከባርነት ነጻ ወጥቶ ክርስትናን የተቀበለ ሰው ስለነበር ሂካም የሱን ስም እንዲወርስ ተደረገ። በዚህም ምክንያት ሂካ ይባል የነበር ወላጆቹ ያወጡለት የልደት ስሙ ወደ ኦነሲሞስ ነሲብ ሊቀየር ችሏል።

**ኦነሲሞስ ነሲብ በስዊዲሽ ሚሲዮን፦**

ኦነሲሞስ፣ ከባርነት ነጻ ወጥቶ በዕለተ ትንሳኤ ተጠምቆ ክርስትናን ሲቀበል ስመ ክርስትናው ኦነሲሞስ ተባለ። ከዚህ በኋላ በምጽዋ 'እምኩሉ' (Émkullu) የስዊዲሽ ሚሲዮን ትምህርቱን መከታተል ጀመረ። ከዚያም ወደ ስዊድን በማቅናት በስቶኮልም Johannelund Missionary Training Institute ለአምስት ዓመታት የሚሽነሪ ስልጠናን ወሰደ።

"The Swedish Mission in Ethiopia» በሚል ርዕስ መፅሐፍ የጻፉት ዓለም እሸቴ እንደገለፁት፤ ቀዳሚዎቹ የሉንድሃል ተማሪዎች ኦነሲሞስን ጨምሮ በቁጥር ስድስት ሲሆኑ፣ ትምህርት ቤቱ፣ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ በካታኪዝም፣ በአጠቃላይ ታሪክ፣ በጂኦግራፊ፣ በአርትሚቲክ እና በቋንቋ (አማርኛ፣ ኦሮምኛ፣ ስዊድንኛ፣ ጀርመን) ተማሪዎችን ያሠለጥናል፤ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስም እንደ እንድ የማስተማሪያ መጽሐፍ ያገለግላል ሲሉ ጽፈዋል።

ኦነሲሞስ፣ ትምህርት በመቅሰም ረገድ ልቡናው




ኦነሲሞስ ነሲብ

ብሩህ እንደ ነበር በትጋቱና ባስመዘገበው ውጤት አሳይቷል። ታዲያ በዚህ ወጣት ውስጥ ያለውን ዕውቀት የመሻት ጉልበት የተገነዘቡ የውጭ አገር መምህራን ልጁን ምፅዋ በሚገኘው የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ብቻ ሊገቱት አልፈለጉም፤ እናም ለበለጠ ትምህርት ባህር ተሻግሮ ይጓዝ ዘንድ እድል ከፈቱለት፡፡

ከስዊድን ስልጠናውን አጠናቆ ወደ ምጽዋ ከተመለሰ በኋላ ኦነሲሞስ ለሚሲዮናዊ ተልዕኮ ወደ ኢትዮጵያ ለመጓዝ ጓዙን ጠቅልሎ ተነሳ። ወደ ኢትዮጵያ ሊያደርግ ያሰበው ጉዞ እንዳሰበው ቀላል አልነበረም። በዚህ ምክንያት በኤርትራ በእምኩሉ የሚሸን ትምህርት ቤት ለረዥም ጊዜ ለመቆየት ተገደደ።

ፕሮሰር ባሕሩ ዘውዴ፣ "Pioneers of Change in Ethiopia" በሰኘው መጽሐፋቸው ላይ በገለጹት መሠረት፤ በወቅቱ አፄ ዮሐንስ በሚሲዮናውያን ላይ አድርገውት በነበረው የእንቅስቃሴ እገዳ ምክንያት ከሰሜን ኢትዮጵያ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመዝለቅ መካከለኛ የአገሪቱን ክፍል ሰንጥቆ መጓዝ የማይደፈር በመሆኑ የነሲሞስ ቡድን አቅጣጫውን በሱዳን በኩል በማድረግ ወደ ወለጋ የመግባትን እቅድ ከአምስት ኢትዮጵያውያንና ከሁለት ስዊድናውያን ጋር አዘጋጀ፡፡

እቅዱንም በተግባር ለመተርጎም ጉዞ ተጀመረ፤ እጅግ ብዙ ተጓዙ። አያሌ በረሃዎችንም አቆራረጡ። በቀይ ባሕር የተደረገውን የባሕር ጉዞ ጨምሮ መንገዳቸው ሁለት ወር ፈጀ። በመጨረሻም ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ድንበር ቢቃረ- ቡም በጊዜው በነበረው የአካባቢ ግጭትና የፀጥታ መታወክ ምክንያት ካሰቡት ሳይደርሱ እቅዳቸው ጨነገፈ።

ታዲያ በመገባደጃው ጠርዝ ላይ የውሃ ሽታ በመሆኑ ሁሉም ጥልቅ ሃዘን ተሰማቸው፤ በእጅጉም ልባቸው ተሰበረ። ሃዘኑ ብቻ ሳይሆን የበረሃው ንዳድ ጠንቅ ፅኑ በሆነ ደዌ ሁሉንም ያስቃይና ያንገላታ ጀመር፤ ከመካከላቸው የቡድኑ መሪ የነበሩ ስዊድናዊው ጂ. ኢ. አርሄኒየስና የኦሮሞው ተወላጅ ወጣቱ ፊሊጶስ በረሐው ውስጥ ሕይወታቸው ሲያልፍ የተረፉት ከብዙ ስቃይና ድካም በኋላ ወደ ምፅዋ ተመለሱ፤ ያም ሆኖ የበረሃው በሽታና መዘዙ ኦነሲሞስንና ትሩፋቱን ለረጅም ጊዜ የሕማም ስቃይ ዳርጓቸዋል፡፡

የመጀመሪያው ጉዞ በእቅዱ መሰረት ባይከናወንም ኦነሲሞስ ተስፋ አልቆረጠም፤ በእምኩሉ የማስተማር ሥራውን ቀጠለ። አብሮም የተለያዩ መጻሕፍትን ወደ ኦሮምኛ ቋንቋ በመመለስ ለተከታዩ ጉዞ ይሰናዳ ጀመር። በዚህ መካከል ማሠልጠኛ ተቋሙ የመንፈሳዊ መጻሕፍትን ኅትመት ለማሳደግ በ1878 ዓ.ም አነስተኛ የማተሚያ መኪና ወደ ኢትዮጵያ በማስመጣት Songs and Psalms (Galata Waaqayoo Gofta Maccaa) የተሰኘው የኦነሲሞስ ሥራ የማተሚያ ቤቱ የመጀመሪያ ሥራ በመሆን የኅትመትን ብርሃን አየ፡፡

ኦነስሞስ ከጀመሪያው ጉዞ ሁለት ዓመታት በኋላ እንደገና ከጥቂት ሰዎች ጋር የሸዋን ግዛት አቋርጦ ወደ ምዕራብ ለማለፍ ጥረት ቢያደርግም የይለፍ ወረቀት በመነፈጉ ወደ እምኩሉ መመለስ ግዴታ ሆነበት። ተደጋጋሚ የሆነው ይህ ስኬት አልባ ጉዞ ብዙዎችን ሲያሳዝን የኦነሲሞስን እምነት ግን በአያሌው ፈትኗል።

ከምጽዋ በመነሣት አንዴ በሱዳን፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በጅቡቲ፣ እንዲሁም በመሀል ሀገር በማድረግ ከሚሲዮናውያኑ ጋር ወደ ወለጋ ለመዝለቅ ያደረገው ያላሰለሰ ጥረት በመሃል አገር ሹሞች መጨናገፉ የኦነሲሞስን ልብ በእጅጉ የጎዳው ሆነ፤ ቢሆንም ተስፋ ቆርጦ ግን አልተቀመጠም።

ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቀውንና እጅግ አድካሚ የሆነውን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ይከውን ጀመር። ቀደም ሲል፣ አራቱ ወንጌላትን ጨምሮ አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በአንዳንድ ፀሐፊዎች አማካይነት ወደ ኦሮምኛ የተተረጎሙ ቢሆንም፣ እንደ ኦነሲሞስ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ለመተርጎም የተነሳ ግን አልነበረም። ኦነሲሞስ፣ ይህን ሥራ ከመጀመሩ አስቀድሞ የተለያዩ መጻሕፍትን የጻፈና ወደ ኦሮምኛ ቋንቋም የተረገመ ነው፤ በወቅቱም አቻና ተስማሚ ቃላትን በማፍለቅ ረገድ ልዩ የቋንቋ ተሰጥኦ በነበራት (በአስቴር ገኖ) በተባለች እንስት ራዳትነት ተግባሩን ከግቡ ሊያደርስ በቅቷል።

ከፍተኛ ጥንቃቄ የጠየቀው ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ሥራ ከፍጻሜ ለመድረስ በርካታ ዓመታትን ወስዷል። የአዲስ ኪዳን ትርጉም ከሰባት ዓመታት ጽኑ ምጥ በኋላ ተወለደ፤ ብዙም ሳይቆይ የብሉይ ኪዳን ትርጉም ተጀምሮ ከብዙ ድካምና ጥረት በኋላ ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ በተፀነሰ በ13ኛ ዓመቱ ለፍሬ በቃ። የመጽሐፉ መጠናቀቅ ለብዙዎች ደስታን ከማጎናጸፍ ባለፈ ለተከታዩ የወንጌል ጉዞ የውስጥ ጥንካሬን፣ በተለይም በገዛ ቋንቋው መጽሐፉ ለቀረበለት ሕዝብ የእውነትና የዕውቀትን ፈለግ በማመላከት ረገድ ዐቢይ የሆነውን ሚና ተጫውቷል።

የኦነስሞስ ወደ ምዕራብ ኢትዮጵያ ለመዝለቅ የተደረገው ተደጋጋሚ ሙከራ ከጊዜ በኋላ እልባት ላይ ደረሰ:: ሙለው የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ተጠናቅቆ እንዳበቃ ኦነሲሞስ ጥቂት ባልደረቦቹን ይዞ ታኅሣሥ 1895 ዓ.ም መንገዱን ወደ አዲስ አበባ አቀና፤ ከረጅምና አድካሚ ጉዞ በኋላ 1896 ዓ.ም መባቻ ላይ አዲስ አበባ ደረሱ።

በወቅቱ አፄ ምኒልክ ወደ ሆለታ ወርደው ስለ ነበር እስኪመለሱ ድረስ አዲስ አበባ ተቀምጦ መጠበቅ ግድ ሆነበት፤ በነዚያ የጥበቃ ቀናት መካከል ግን ሥራ ፈቶ አልተቀመጠም፤ የወቅቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ፓትርያርክ አቡነ ማቴዎስ ዘንድ በመቅረብ፣ «የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች» የተሰኘ ሥራውን አበረከተ:: አቡኑም፣ «መልካም! መልካም!» የተሰኘውን ቃል ሰነዘሩ። ቀጥሎም በኦሮምኛ የተተረጎመውን መጽሐፍ ቅዱስ አቀረበ። ንጉሡ ወደ አዲስ አበባ እስኪመለሱም አቡኑን በተደጋጋሚ በመጎብኘት ስለ መንፈሳዊ ጉዳይ አውግተዋል።

አፄ ምኒልክ ወደ አዲስ አበባ እንደተመለሱ አቡነ ማቴዎስ፣ ኦነሲሞስ ነሲብ የመጣበትን ጉዳይ ለንጉሡ ያቀርብ ዘንድ ሁኔታውን አመቻቹ። ኦነሲሞስም ወደ ወለጋ ዘልቆ ለማስተማር የሚያስችለውን ፈቃድ ያገኝ ዘንድ ንጉሡን ጠየቀ። ከመጀመሪያው እትም አንዱ የሆነውን የኦሮምኛ መጽሐፍ ቅዱስ ለአፄ ምኒልክ ገፀ በረከት አቀረበላቸው። ንጉሡም በደስታ ተቀበሉ። ወደ ወለጋ ሄዶ እንዲያስተምርም ተፈቀደለት።

ኦነስሞስ ወለጋ መግባቱ፣ እንዲሁም የቀለምና የሃይማኖት ትምህርትን ለማስተማር እድል በማግኘቱ ደስተኛ ሆኖ ለጥቂት ጊዜያት ቢቆይም በእምነቱ ሳቢያ የደረሰበት ስደት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሣ ተቃዋሚዎቹ ከወለጋ አዲስ አበባ እያመላለሱ ሙግት ከመግጠምም አልፈው ንብረቱ እንዲወረስና በእግረ ሙቅም ታስሮ ወህኒ እንዲወርድ አድርገውታል። በአጭሩ ኦነሲሞስ ለእምነቱም ሆነ ለነፃው ኑሮ አንጻራዊ ዕረፍት ያገኘው በ1909 አካባቢ ከልጅ ኢያሱ ባገኘው የእምነት ነጻነት በኋላ ነበር።

ኦነሲሞስ፣ ከወንጌል ሥራው በተጓዳኝ የቀለም ትምህርት እንዲሁም ከነበረው መጠነኛ የሕክምና እውቀት በመነሳት ሕሙማን በነጻ ያገለግል ነበር። ምንም እንኳ መደበኛ ትምህርት ቤት ባይኖርም፣ ኦነሲሞስ የባላባት ልጆችን በመሰብሰብ መጻፍና ማንበብ ማስተማር ቀጠለ። በርካታ ልጆችም በአማርኛ የተጻፉ የወንጌል ክፍሎችን ለማንበብ በቅተዋል፤ ይህም ኦነሲሞስ በማኅበረሰቡ ዘንድ የነበረውን መከበር ከፍ አድርጓል፡፡

ታዲያ በነዚህ ሁሉ ማኅበራዊና መንፈሳዊ ትግሎች መካከል በጽናት የተራመደ፣ ስደት፣ ግዞትና መገፋት ቢፈራረቁበትም እስከ መጨረሻዋ ርምጃ ድረስ የተጓዘ፣ ራሱንም ለሰው ልጆች ሁለንተናዊ ለውጥ የሰጠው፤ ከአገሩ ከወጣ ከሰላሳ አምስት ዓመታት በኋላ የአከባቢውን ልጆች በእውቀት ብርሃን አይናቸው እንዲገለጥ ብዙ ጥረት ያደረገው ኦነሲሞስ፤ ከዚህ ዓለም በሞት የተለየው ነቀምቴ ወለጋ ሳለ በሰማንያ አንድ ዓመቱ ነበር።

እኛም ለሕዝብና ለሀገራቸው መልካም ያደረጉና እንዲሁም በተሰማሩበት ዘርፍ ሁሉ የማይነጥፍ አሻራ ማኖር ለቻሉ ግለሰቦች ታሪካቸውን በመጥቀስ ለአበርክቷቸው ክብር እንሰጣለን። በዚህ የባለውለታዎቻችን ዓምድ ላይም ለአንባቢያን እናቀርባለን። እውቁ የመፅሐፍ ቅዱስ ተርጓሚ ኦነስሞስ ነሲብንንም ላበረከቱት አስተዋጽኦ አመሰገንን። ሰላም!

ለዚህ ፅሑፍ እንደ ምንጭነት የተለያዩ ማህበራዊ ድረ-ገፆችን ተጠቅመናል።

# ስፖርት

## በአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና የሚሳተፈው ቡድን ዛሬ ወደ ዱዋላ ይጓዛል

**ዓለማየሁ ግዛው**

በ23ኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና የሚሳተፈው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን ለውድድሩ የሚያደርገውን ዝግጅት አጠናቆ ዛሬ ወደ ካሜሮን ያቀናል። የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ለቡድኑ ሽኝት ያደረጉ ሲሆን፤ የስራ መመሪያና የባንዲራ ርክክብ ሥነሥርዓትም ተከናውኗል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን ከሰኔ 14 እስከ 19/2016 ዓ.ም በካሜሩን ዱዋላ አስተናጋጅነት በሚካሄደው 23ኛው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና ለመሳተፍ ዛሬ ወደ ሥፍራው የሚያቀና ይሆናል። ብሔራዊ ቡድኑ ለ15 ቀናት ተሰባስቦ ዝግጅቱን ሲያደርግ ቆይቷል። ቡድኑ በሩጫ፣ ዝላይና ውርወራ ከሚካሄዱት 45 የውድድር ተግባራቶች መካከል በ41ዱ ይሳተፋል። ከነገ በስቲያ በሚጀመረው ትልቁ የአህጉሪቱ የአትሌቲክስ የውድድር መድረክ 34 ሴት እና 43 ወንድ በአጠቃላይ 77 አትሌቶች፣ በ15 አሰልጣኞች እየተመሩ በውድድሩ ውጤት ለማስመዝገብ ጠንካራ ፉክክርን እንደሚያደርጉም ይጠበቃል።

ለሁለት ሳምንታት በዝግጅት ላይ የቆየው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ቡድን ከትናንት በስቲያ ይፋዊ ሽኝትም ተደርጎለታል። በሽኝት መረሃግብሩ ላይም የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ እና የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች የተገኙ ሲሆን፤ ብሔራዊ ቡድኑ ውጤታማ እንዲሆን የማበረታታትና የባንዲራ ማስረከብ ሥነሥርዓትም ተከናውኗል። የዝግጅት ጊዜው አጭር ቢሆንም ውጤት ለማስመዝገብ እንደሚሄዱ የጠቆሙት የቡድኑ አትሌቶችና አሠልጣኞች፤ ለቡድኑ



**በአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና የሚሳተፈው የኢትዮጵያ ቡድን ጥሩ ውጤት ለማስመዝገብ ቃል ገብቷል፣**

ጥሪ ከተደረገበት ጊዜ አንስቶ ለውድድሩ የሚያበቃ ዝግጅት ሲያደርጉ መቆየታቸውን ተናግረዋል። የዘንድሮውን ውድድር ለየት የሚያደርገው ኢትዮጵያ በሁሉም የውድድር ተግባራት የምትሳተፍ በመሆኑ በማትታወቅባቸው ውድድሮች ልምድን በመቅሰም በዓለም ቻምፒዮና የመሳተፍ እድል ሊፈጠር ስለሚችልም ነው። ፌዴሬሽኑም አስፈላጊውን እገዛ ሲያደርግ ቆይቷል።

እአአ የ2022ቱ የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና አዘጋጅ የነበረችው የሞሪሺየሷ ሴንት ፒሬ ስትሆን፤ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን 14 ሜዳሊያዎችን ሰብስቦ 5ኛ ደረጃን በመያዝ ነበር ያጠናቀቀው። ዱዋላ ላይም ከዚህ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ተሳትፎውን ያደርጋል። በነበረው የአጭር ጊዜ ዝግጅት ሁሉም አሠልጣኞችና አትሌቶች ዝግጁና ብቁ በመሆናቸው የተሻለ ውጤትን አስመዝግበው ለመመለስ ጥረት እንደሚያደርጉም ተናግረዋል። አትሌት ዘገየ ሞጋ እና አትሌት ውብእርስት አስቻለው፤ ለሀገራቸው ውጤት ለማስመዝገብ ጥረት እንደሚያደርጉ ጠቁመዋል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ረዳት ኮሚሽነር ደራርቱ ቱሉ ከሁለት ዓመት በፊት ሞሪሺየስ በተካሄደው የአፍሪካ አትሌቲክስ ቻምፒዮና አጥጋቢ ውጤት መመዝገቡን አስታውሳ፤ በዚህ ውድድር የመዘጋጃ ጊዜው በቂ ባይሆንም የመተዋወቅና ቅድመ ዝግጅት መደረጉን ገልጻለች። ውድድሩ ኢትዮጵያ ለኦሊምፒክ እየተዘጋጀች በምትገኝበት ወቅት መሆኑ ታሪካዊና ልዩ የሚያደርገው ሲሆን፤ አሠልጣኞችና አትሌቶች በመተባበርና በመተጋገዝ የተሻለ ውጤት ለማምጣት እንደሚተጉ እምነቷ መሆኑንም ተናግራለች።

የኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ዶክተር አሸብር ወልደጊዮርጊስ በበኩላቸው፤ ዓመቱ በውድድሮች መብዛት ለኦሊምፒክ ኮሚቴና ለአትሌቲክስ ፌዴረሽን እጅግ ከባድና ፈታኝ እንደነበር ገልጸዋል። ይህንን በብቃት በመወጣት ብቁ አትሌቶችን እና አሠልጣኞችን መመልመል ትልቅ ጥንካሬን ይጠይቃል፤ በመሆኑም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ላሳየው ብቃትና ጥንካሬ ምስጋና አቅርበዋል። ሁሉም አትሌት ህልሙ በውድድሮች ውጤትን ማምጣት እና በኦሊምፒክ መሳተፍ በመሆኑ እንደዚህ ዓይነት ውድድሮች መነሻ ናቸው። ውድድሩ ትልቅ ጥንካሬን የሚጠይቅና ፈታኝ እንደመሆኑ፣ አትሌቶች የተለመደውን የአሸናፊነት ሥነ ልቦናን በመላበስ በድል እንደሚመለሱ እምነታቸው እንደሆነም አንስተዋል። ከ120 ሚሊዮን ሕዝብ ተመርጦ ሀገርን መወከል ትልቅ እድል መሆኑን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቱ መደጋገፍ እንደሚያስፈልግና ኦሊምፒክ ኮሚቴም ከጎናቸው መሆኑን ገልፀዋል። ልዩነት እንደማያስፈልግ እና ጠንክሮና ተባብሮ አንዱ የአንዱን ቀዳዳ በመሸፈን ኢትዮጵያን ከፍ ማድረግ እንደሚያስፈልግም አመልክተዋል፡፡

ከተመሠረተ ቅርብ ጊዜ የሆነውና አትሌቶችን ለማበረታታት እንዲሁም ጥሩ ውጤት እንዲመጣ የማይናቅ ሚናን በመጫወት ላይ የሚገኘው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ደጋፊዎች ማህበርም እንዲሁ ወደ ሥፍራው በማቅናት ቡድኑን እንደሚያበረታታ ተገልጿል። ከቡዳፔስቱ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ጀምሮ ድጋፉን ሲያደርግ የቆየው ማህበሩ 20 የሚደርሱ ልዑካንን ወደ ሥፍራው ለመውሰድ ጥረት እያደረገ መሆኑን አስታውቋል፡፡


## የጨረታ ማስታወቂያ ጨረታ ቁጥር ድ/አ/ኤ/አ/ግ/ጨ/003/2016 (ሎት-1 እና ሎት-2 )

የድሬደዋ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት በተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት /በጋራዥ/ ስራ ላይ የተሰማሩ እና ብቃት ያላቸው ተቋማት/ድርጅቶችን በማወዳደር የድርጅቱ ንብራት የሆኑትን ተሽከርካሪዎች/መኪኖችን ለአንድ ዓመት በሚቆይ በውል ማሰራት ይፈልጋል፡፡

| ሎት | የዕቃው ዓይነት | የጨረታ መዝጊያ ቀን | የጨረታ መክፈቻ ቀን | የጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ |
|---|---|---|---|---|
| ሎት-1 | የተለያዩ የቀላል ተሽከርካሪ የጥገና አገልግሎት ግዥ | ሐምሌ 2 ቀን 2016 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት | ሐምሌ 2 ቀን 2016 ዓ.ም 4፡30 ሰዓት | ብር 7,300.00 |
| ሎት-2 | የተለያዩ የከባድ ተሽከርካሪ የጥገና አገልግሎት ግዥ | | | ብር 7,300.00 |

1. በፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሰጠ ደረጃውን የሚገልፅ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ፡፡
2. ማንኛውም በዘርፉ የተሰማራ የታደሰ የንግድ ፈቃድና የስራ ፍቃድ ማቅረብ የሚችሉ፡፡
3. የዘመኑን ግብር የከፈሉ
4. የተጨማሪ.እ.ታ፣ የግብር ከፋይ መ/ቁጥር ማቅረብ የሚችሉ
5. ተጫራቾች መኪኖች ብልሽት በገጠማቸው ቦታዎች ድረስ በመሄድ ለመጠገን ፍቃደኛ መሆናቸውን በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡
6. ተጫራቾች በስራ ቀን፤ በባዕላት ቀን ፤በሳምንቱ የዕረፍት ቀናት ስራውን ለመስራት ፍቃደኛ መሆናቸውን በፅሁፍ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፡፡
7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ማስታወቂያው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለሎት-1 እና ለሎት-2 እያንዳንዳቸው ብር 300(ሶስት መቶ) የማይመለስ በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
8, አድራሻ፡- ድሬደዋ ግሪክ ካንፕ የድሬደዋ ስታዲየም አጠገብ በሚገኘው የድሬደዋ ኤሌክትሪክ አገልግሎት ግዥ፣ ሎጀስቲክስ፣ ዌርሀውሲንግ እና ፋሲሊቲ ቢሮ ቁጥር 206/207፣
9. ተጫራቾች ለጨረታ ዋስትና ማስከበሪያ የሚያቀርቡት የገንዘብ መጠን ከላይ በሠንጠረዡ ውስጥ በተገለፀው መሠረት ሆኖ በባንክ በተረጋገጠ ቼክ/CPO/ ወይም በቅድመ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ለስድስት ወራት የሚያገለግል የባንክ ዋስትና (Bid Bond) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
10. ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሰነዳቸውን በሰም በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ፋይናንሻል «ኦሪጅናል እና ኮፒ » በማለት በተለያየ ፖስታ በማሸግ እና ሁለቱን በአንድ ትልቅ ፖስታ በማድረግ ጨረታ ቁጥር ድ/አ/ኤ/አ/ግ/ጨ/003/2016 ሎት-1 እና ሎት-2 የሚል ምልክት በማድረግ ሎት-1 እና ሎት-2 እስከ ሐምሌ 2 ቀን 2016 ዓ.ም 4፡00 ሰዓት ድረስ ከላይ በተጠቀሰው አድራሻ ለዚሁ ጨረታ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት የሚኖርባቸው ሲሆን ጨረታው በተመሳሳይ ቀን ከጠዋቱ 4፡30 ሰዓት የሚከፈት ይሆናል፡፡
11. ተጫራቾች ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ በስልክ ቁጥር **025-211-00-23/025-112-98-45** በመደወል ወይም ቢሮ ቁጥር 206/207 በአካል በመቅረብ ማግኘት ይችላሉ፡፡
12. ጨረታው ከላይ በተገለፀው መሠረት ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፣
13. ድርጅቱ የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## የድሬደዋ አስተዳደር ኤሌክትሪክ አገልግሎት